


አ.አ ከተማ በሰሜን ምሥራቅ የሚገኘው የደብረ ከዋክብት ቤተ ክርስቲያን



የደብረ ሰሞስው ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን



www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንግኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።»

ዋና አዘጋጅ
ሊቀ ኅሩያን ልሣነ ወርቅ በዛብኅ
ም/አዘጋጅ መ/ክንፈ
ርግብ ማርቆስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ሣ·ቁ· 3137
አዲስ አበባ ፡

## ማውጫ

**አርእስት** **ገጽ**

ደብዳቤዎች ……… ፩
ርእስ አንቀጽ ……… ፪
የብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ ቃለ ቡራኬ ……… ፬
አዲስ ዘመን ……… ፭
ለአ ማር አይጥመውም ……… ፮
ዜና ሊቃውንት ……… ፯
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ……… ፲
የዐባቴ አያሌው ረታ ታሪክ በአጭሩ ……… ፲፪
የደብረ ስዋስው አደሬ ቅኔ ጓን ምሕረት ታሪክ ……… ፲፬
ልማት በደብረ ከዋክብት ……… ፲፮
ዜና ሞት ዘማሪ ጌታ አቦዬ ……… ፲፯
የዋይታ ድምፅ ……… ፳
ጤናችን ……… ፳፪
ጸሎተ ክረምት ……… ፳፫

## ደብዳቤዎች

ለትንግኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ ፡

በቅድሚያ እንኳን ለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለፍልሠታ ጾም አደረሣችሁ (አደረሠን) ከሰላምታዬ ቀጥዬ የሚቀርቡ ጥያቄዎች የሚከተሉት ይሆናሉ ። ይኸውም ፡

፩· ሰዎች ጾም እንጾማለን ይላሉ ነገር ግን በቤት ተነሥተው የጾም ምግብ ይመገባሉ ከመብላት የተቆጠቡት ሥጋንና ቅቤን እንጅ ሌላውን አልተውትም ይህ እንደ ጿሚዎች ይቆጠርላቸዋልን ።

፪· ጾም መጾም ያለበት ከስንት ሰዓት እስከ ስንት ሰዓት ነው?" ። የዚህን ምላሽና ጥቅስ ብትጠቅሱልኝ ።

፫· ሰዎች እኛ ልጅ ነን መጾም የለብንም ይላሉ ማንኛውም ሕዝበ ክርስቲያን መጾም ያለበት ከስንት ዓመት በላይ ሲሆን ነው?

፬· አንድ የንስሐ አባት ቄስ ይንስሐ ልጅ መያዝ ያለበት ብዛት ከስንት እስከ ስንት ነው? በየትኛው መጽሐፍ ነው የሚገለፀው ? መጻሕፉንና ቁጥሩን ብትገልጹልኝ ።

፭· የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታዮች በአንገታችን ክር እናስራለን ይህ ክር መታሰር የተጀመረ መቼ ነው ጌታ ከተጠመቀ ወዲሕ ነው ወይንስ ከዚያ በፊት ከሆነ ምክንያቱን ብትገልፁልኝ?

፮· ከኦርቶዶክስ ሃይማኖትና እስላም ሃይማኖት ቅድሚያ የነበረው የትኛው ነው? ወይንስ አብሮ የነበረ ነው? የተለያየ ከነበረ እንዴት ሊለያዩ እንደቻሉ ብትገልፁልኝ?

፯· ዕረቡና ዓርብን መጾም የጀመረው ማን ነው?

እነዚህን ሁለት ቀኖች የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮችም እንጾማለን እስላሞችም በነዚህ ሁለት ቀኖች መስኪድ በመሰብሰብ በመስገድ ጸሎት በማቅረብ ሲማፀኑ ይውላሉ በነዚህ ሁለት ቀኖች የሚያለያየን ምንድን ነው? ብትገልፁልኝ ።

፰· እንደምናውቀው ባገራችን ብዙ የመናፍቃን ሃይማኖቶች እየተስፋፉ ናቸው ። እነዚህ ሃይማኖቶች ከኦርቶዶክስ ሃይማኖት እና ከእስላም ሃይማኖት ሌላዎቹ ድሮም ነበሩ ወይንስ በቅርብ ገዜ ነው የመጡት እንዴት እንደመጡና የት እንደነበሩ እንዴትስ እንደተጀመሩ ብትገልጹልኝ ።

፱·እንደቤተ ክርስቲያናችን ደምብና ትዛዝ ወንዶች በምሬብ ሴቶች በደቡብ እንዲገቡ ታዟል ነገር ግን በአዲስ አበባ ሁሉም ተቀላቅሎ ይገባል ካህናቶችም ቢናገሩ ሰዎች አላወቁም ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ።

፲· ግማሽ ቅዳሴ ላይ ይኸውም ወንጌል እንደተነበበ ትምህርት ይሠጣል ቅዳሴ አቋርጦ ትምህርት መስጠት እንዴት አስፈለገ? ምክንያቱን ብትገልጹልኝ ።

፲፩· እንደምታውቁት ባለፈው ወር አካባቢ አንዲት ልጅ ራእይ አየሁ ምልክቱንም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጠጉር ታገኛላችሁ አለች እየተባለ ሲወራ ከረመ እንደገና ባልማማት አንድ ወንድማችን በዚህ ቀን ዓለም ታልፋለች እንዲሁም ነሐሴ ፳፰ ቀን ከሰማይ እሳት ይወርዳል እመቤታችን ነግራኛለች በማለት ሲናገር ሰምቻለሁ ይህ ምን ያህል እውነተኛነት አለው? ብትገልጹልኝ ።

፲፪· የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፳፬ ቁጥር ፳፫ በዚያ ጊዜ ማንም እነሆ ክርስቶስ ከዚህ አለ ወይም ከዚያ አለ ቢላችሁ አትመኑ ሐሠተኞች ነቢያት ይነሣሉና ይላል ይህ ምን ማለት እንደሆነ ብትገልጹልኝ?

ተማሪ ፍሥሐ ሲሳይ

**መልስ ፡**

የሰላም መልስ ሰላም ነውና የእግዚአብሔር ሰላም ከሁላችን ጋር ይሁን ላቀረብካቸውም ጥያቄዎች መልስ ይኸው ።

፩ኛ/ደረቅ እንጀራ ማልደው ከመኝታቸው ተነሥተው ከበሉ ጾዋሚዎች ናቸው ተብለው ሊቆጠርላቸው አይችልም ዋና ፍሬ ነገሩ ጾም ማለት ጥዋት ባለ መብላት ለእግዚአብሔር መገዛት ነው። ኃጢአት የተጀመረውና አዳምና ሔዋን የተፈረደባቸው ሥጋ በልተው አልነበሩም የበሉት የእንጨት ፍሬ ነው አሁንም ቢሆን ሥጋን አልበላም ደረቅ እንጀራን ግን በጥዋት እበላለሁ የሚል ሰው ቢኖር ሕገ ጾም አፍራሽ እንጂ ጾዋሚ አለመሆኑን እናረጋግጥልሃለን ። ፪ኛ ጾም የተለያየ ሰዓት አለው ይኸውም ጾመ ሕርቃል ፲፪ ሰዓት

ዓቢይ ጾም ፲፪ ሰዓት ሰሙነ ሕማማት ከሌሊቱ አንድ ሰዓት ጨምሮ ፲፫ ሰዓት ሲጾም ሌሎች አጽዋማት ማለት ዓርብና ረቡዕ የገና ጾምና የሰኔ ጾም እንዲሁም ጾመ ፍልሰታና የነነዌ ጾም ሁሉ እስከ ዘጠኝ ሰዓት መጾም እንደሚ

(ወደ ገጽ ፫ ዞሯል)



www.ethiopianorthodox.org

# ርእሰ አንቀጽ

# ሐሜትና ነጎርጓር

ሐሚት በውሸት መናገርና ያልተደረገውን እንደተደረገ እያደረጉ ማስረጨት ሲሆን ነጉርጓር ደግሞ የሚያሙትን ሐሜት ለመግለጽ እየፈለጉ ሰሙኝ አልሰሙኝም በማለት በቀስታ እርስ በእርስ መነጋገር ነው ሁለቱም በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠሉ ነገሮች ናቸው ።

ቀደም ያሉ ታሪኮችን ብንመለከት ሕዝበ እስራኤል በሐሚትና በነጎርጓር እንደ ተጉዱ ከእግዚአብሔርም እንደራቁ እንረዳለን እስራኤላውያን በረኃብ ምክንያት ወደምድረ ግብፅ ወርደው ፬፻፴ ዘመን መኖራቸውን ከታሪክ እንረዳለን በእነዚህ ዘመናት ብዙ ግፍ ተፈጽሞባቸዋል ዘራቸው ከግብፃውያን ይልቅ እየበዛ በመሄዱ ክባድ ከባዱን ሥራ እንዲሠሩ የሚገደዱት እስራኤላውያን ነበሩ ይህም የሚደረገው ከድካም የተነሣ ብዛታቸው ይቀነሣል በሚል አስተሳሰብ ነበር እነርሱ ግን በፈቃደ እግዚአብሔር እየበዙ ይሄዱ ጀመር ወንድ ሲወለድ እያነቁ ወደ ባሕር ይጥሉ ጀመር በዚያ ዘመን ሙሴ ተወለደ ዓቀብተ መወልዳኑ ለጊዜው ስለአሳዘናቸው ተተውት ሄዱ ይሁን እንጂ ወላጆቹ ወስደው በባሕር ዳር አስቀምጠውታል ፡ በዚያም ሳለ አገዳ ሰበር (ግልገል አንሳ) የሚባል አሞራ እንዳይበላው ቀን ቀን እህቱ እንጨት የምትለቅም እየመሰለች ስትጠብቀው ትውላለች ሌሊት ደግሞ ወላጅ እናቱ እየመጣች ስታጠባው ታድር ነበረች ።

ከዕለታት አንድ ተርሙስ የምትባለው የፈርዖን ልጅ ሰውነቷን ለመታጠብ ወደ ወንዝ ወርዳ ሳለች የተቀመጠበትን ሣጥን አግኝታ ይዛው ወደቤት ሄደችና ብትከፍተው ልጅ ሆኖ አገኘችው ልጅ አልነበራትም ነበርና በጥሩ ሁኔታ እየተንከባከበች አሳደገችው ስሙንም ሙሴ ብላ ሰየመችው ከውሀ ዳር የተገኘ ማለት ነው ካደገ በኋላ የወገኖቹን የእስራኤልን ጥቃት ሲመለከት በጣም ይናደድ ነበር ወገኖቹንም ከባርነት ቀንበር ለማላቀቅ ከፍ ያለ ምኞት ነበረው እግዚአብሔርም ምኞቱን ተመልክቶ እስራኤል ወገኖቹን ከባርነት አውጥቶ ወደ ሀገራቸው እንዲያስገባቸው መረጠው ፡ በእግዚአብሐር ፈቃድ ልዩ ልዩ ተአምራትን በማድረግ ከባርነት ቀንበር አላቀቃቸው ሕዝበ እስራኤል በእግዚአብሔር ቸርነት በሙሴ መሪነት ከግብፅ ከወጡ በኋላ ትንሽ ችግር ቢደርስባቸው በመታገሥ ፈንታ በእግዚአብሔር ላይ አንጉራጉሩ ።

መና ከደመና እያወረደ እየመገባቸው ከደጋ ውርጭ አይታጣምና መና አወረድኩላችሁ ይሉናል እንጂ በበረሃ ቢሆንማ መቼ ይቻለው ነበር እንዲሁም ከጭንጫ ውሀ አይጠፋምና አፍልቆ አጠጣኋችሁ ይሉናል ። እንጂ በቆላ ቢሆንማ መቼ ይችል ነበር በማለት እግዚአብሔርን አሙት በሙሴ ላይም አንጉራጉሩ "ብፁዕ ዘይበልዕ እምፍርፋሪት ማዕዱ ለፈርዖን ወሚ ይሢኒ ዘይሰቲ ማዕገቲሃ ለግብፅ "ከፈርዖን ፍርፋሪ ለቃቅሞ የሚበላና ከግብፅም ምንጮች ውሀ የሚጠጣ እጅግ የተመሰገነ ነው ሙሴና አሮን! አንውጣ አንውጣ ብላችሁ አስወጥታችሁ በረኃብ ልትገድሉን ብለው አማረሯቸው ።

እግዚአብሔር የሕዝቡን ሐሚትና ነጎርጓር ሰምቶ ሙሴን ጠራና "አውርዖሙ ቀላተ ሐራሲዮን" ሐራሲዮን ወደተባለው በረሃ ይዘሃቸው ውረድ አለው ይዟቸው ወረደ ምግቡ አልቀረባቸውም መና ከደመና እየወረደላቸው በልተዋል ከጭንጫ ውኃም እየፈለቀላቸው ጠጥተዋል ነገር ግን ነዘር የሚባል እባብ ተነሥቶ እየነደፈ ይፈጃቸው ጀመር በዚህ ጊዜ ሙሴ ወደፈጣሪው ቢያመለክት እባቡን አስመስለህ ናስ ሥራና በእንጨት ላይ ሰቀለህ ምታው በሽታው ያልጸናበት መጥቶ መልኩን አይቶ ይዳን የጸናበት ድምፁን ብቻ ሰምቶ ይዳን አለው እንደታዘዘው አደረገ ያልጸናበት መጥቶ መልኩን በማየት የጸናበት ድምጹን በመስማት ብቻ ተፈውሷል ። ይህ ሁሉ በሐሚትና በነጉርጓር ከፍተኛ መከራ የሚድረስ መሆኑን የሚያስረዳ ነው ።

በተጨማሪም ሙሴና አሮን ታላቅና ታናሽ ናቸው አሮን ታላቅ ሲሆን መንፈሳዊ አገልግሎቱን የሚመራ ነበር ሙሴ ደግሞ ታናሽ ነው በሥጋዊ አስተዳደር ተወክሎ ሕዝቡን የሚያስተዳድር ነበር በአገልግሎታቸው ላይ ስሕተት ሳይኖርባቸው አንዳንድ ተንኮለኞች ቀንተው በምቀኝነት ተነሡባቸው ሁለቱ ወንድማማቾች ሥጋዊውንም ሆነ መንፈሳዊውን ሥልጣን ይዘው ሲያዝዙን ሊኖሩ ነውን ? እኛስ የበኩሩ የሮቤል ልጆች አይደለምን ? ብለው ደቂቀ ሮቤል በሙሴ ደቂቀ ሌዊ በአሮን ላይ ተነሡባቸው በመጀመሪያ በሙሴ ዳኝነት አሮንን መክሰስና የእርሱን ሥልጣን መያዝ አሰቡን ከዚያ በኋላ ወደ ሙሴ እንሄዳለን አሉና የአሮንን ሥልጣን እንዲሰጣቸው ሙሴን ጠየቁት ሙሴም አሮን የተሾመው ከእግዚአብሔር አግኝቶ ነውና እናንተም ከእግዚአብሐር ጠይቃችሁ ተሾሙ ቢላቸው ያደላብን መስሏቸው ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ማዕጠንተ ወርቅ ይዘው ሊያጥኑ ገቡ ጢሰ ቀታሬው ቢነካቸው በቁማቸው እንደተለበለበ ግንድ ሆኑ ፡ የቀሩት ሰዎች ይህንን ሁሉ የሚያደርጉን ሙሴና አሮን ወደፈጣሪያቸው እያመለከቱ ነው ብለው በደንጊያ ወግረን በእሳት አቃጥለን እንገድላቸው ተባብለው ወደ ሙሴና አሮን ሲመጡ ዳታንና አቤሮንን ከእነተከታዮቻቸው ምድር ተከፍታ ዋጠቻቸው ቀሬም ምክር ለመጽናት ሄዶ በዚያው ተሰጥሞ ቀርቷል ።

ይህ ሁሉ የሐሚትና የማንጉራጉር የምቀኝነትና የተንኮል ውጤት መሆኑን ሁላችንም ልንረዳው ይገባናል ክቡር ዳዊትም በመዝሙሩ ። "ዘየሐሚ ቢጸ በጽሚት ኪያሁ ሰደድኩ" ባልንጀራውን በቀስታ የሚያማውን እርሱን አሳደድሁ ብሏል መዝ ፻ ቁ ፭ ስለዚህ በእግዚአብሔር አምነን በሕጉ የምንመራ ሁሉ ሐሚትንና ነጉርጓርን አስወግደን በፍቅር በሰላም በትሕትና ሆነን ፈጣሪያችን እናመስግነው የጉደለውን ይሞላልናል የተዛባውን ያስተካክልልናል የምንፈልገውንም ይሰጠናል አምላካችን ሁሉን ለማድረግ የማይሳነው ክሃሊ አምላክ ነውና ።

## ይብዳ…

(ከገጽ ፩ የዞረ)

ገባ የቤተ ክርስቲያናችን ሕግና ሥነ ሥርዓት የሚያዘው ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፲፭ ያገዛል ያንን መመልከት ነው ፡

፫ኛ/ ማንኛውም ክርስቲያን ከ፯ ዓመት በላይ መጾም ይገባዋል።

፬ኛ የንሥሐ አባት ማስተማር የሚቻለውን መያዝ ይችላል ነገር ግን መምከር ማስተማር የማይችል ከሆነ አንድን ሰውም ቢሆን መያዝ አይገባውም ምክንያቱም በመምህረ ንሥሐነት የያዛቸውን ልጆቹን ካልመከራቸው ካላስተማራቸው ለእግዚአብሔር ሊገዙ ሃይማኖታቸውን ሊያውቁ ስለማይችሉ ተበትነው ስለሚጠፉ ማስተማር የማይቻለው ቄስ የንሥሐ ልጅ መያዝ ተገቢ አይደለም ስለ ዚህ ወሳኙ ማስተማሩ ነው ።

፭ኛ/ክር በአንገት ማሠር የተጀመረው ከልደተ ክርስቶስ ወዲህ ነው እንጂ ከክርስቶስ በፊት ክር አለነበረም ይኸውም ለአማኒና ለኢአማኒ የመለያ ምልክት ነው ።

፮ኛ ከኦርቶዶክስና ከእስልምና ሃይማኖት ቅድሚያ ያለው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ነው ምክንያቱም የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ጌታ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመሠረተው ሲሆን ከተመሠረተም እንሆ በኢትዮጵያ አቆጣጠር ፲፱፻፹፩ ዓመት ሁኖታል የእስልምና ሃይማኖትን የመሠረተ ግን መሐመድ ሲሆን መሐመድ የተነሣውም በ፯ኛው መቶ ክ/ዘ/ነው ይባላል ።

ስለዚህ በ፯ኛ ዘመን ይቀድመዋል ማለት ነው ልዩነቱም ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ብላ ስታምን መሐመድ ግን ክርስቶስን አምላክ ብሎ አለማመኑ ነው ይህ ነው ልዩነቱ ፡

፯ኛ/ ዓርብንና ረቡዕን መጾም የጀመሩት ሐዋርያት ናቸው ይህን ንም መረዳት የሚቻለው አንድ ጊዜ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ስለጾም እንስተው እኛ እንጾማለን ደቀ መዛሙርትህ ግን ለምን አይጾሙም ብለው ቢጠይቁት ጌታ ሚዜዎች ሙሽራው ከእነርሱ ጋር ሳለ ሊያዝኑ ሊጾሙ ይችላሉን? ካላቸው በኋላ ፡ ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ጊዜ ይመጣል ያን ጊዜ ይጾማሉ ብሎ እንደ መለሰላቸው ማስተዋል ነው ጌታ ከሐዋርያት የተለየበትም ዓርብ መሆኑ ነው በዚህ ምክንያት እንደምንጾም እንገልጽልሃለን ማቴ ፱፡፲፬፡፲፭ እስላሞችም በእነ ዚህ ቀኖች ይሰግዳሉ ስለ ምት ለው ግን እነሱ ለምን እንደሚያከ ብሩዋቸው መጠየቅ ነው ።

፰ኛ በ፰ንተኛው ተራ ቁጥር የጠቀስከው ብዙ ሐተታ የሚያስ ፈልገው ነው ቢሆንም ባጭሩ እን ደላከው በሀገራችን ብዙ መናፍ ቃን አሉ ።

እነዚህ የተለያዩ ሃይማኖቶች ከኦርቶዶክስ በኋላ የተደራጁ እንጂ በፊት የነበሩ አይደሉም ነገር ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስ ቶስ ስለ እነዚህ መናፍቃን ብዙ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ነበር የሰጠ ውም ማስጠንቀቂያ ፩ኛ ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ የእኔን

(ወደ ገጽ ፲፫ የዞረ)





www.ethiopianorthodox.org

# የዘመንን መለወጫ በዓል ምክንያት በማድረግ ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ ያስተላለፉት ቃለ ቡራኬ

ስብሐት ለእግዚአብሔር ለዘአብጽሐነ እስከዛቲ ሰዓት — እስከዚህ ዕለትና ሰዓት ላደረሰን አምላክ ክብርና ምስጋና ይሁን ።

በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር መስከረም አንድ ቀን የአዲስ ዓመት መባቻ እንደ መሆኑ መጠን ይህን ዓውደ ዓመት እንኳን በደኅና አደረሳችሁ ። ቅዱስ መጽሐፍ "ዚአከ ውእቱ መዓልት፡ ወዚአከ ይዕቲ ሌሊት ፡ አንተ ፈጠርከ ፀሐየ ወወርኀ ወአንተ ገበርከ አድባረ ምድር ኩሎ ፡ ክረምተ ወሐጋየ ዘአንተ ፈጠርከ፡ ወተዘከር ዘንተ ተግባረከ" — ቀኑ ምሌሊቱም ያንተ ነው ፡ አንተ ፀሐይንና ጨረቃን አዘጋጀህ ፡ አንተ የምድርን ዳርቻ ሁሉ ሠራህ፡ በጋንና ክረምትን አንተ አደረግህ ፡ ይህን ፍጥረትህን አስብ" ።

ሲል እንደተናገረው መዓልትና ሌሊት ፡ ክረምትና በጋ የሚፈራረቁት ፡ ነፋሳት የማነፍሱት ዝናማት የሚዘንቡተ ማየት የሚፈሱት በእግዚአብሔር ሠራዒ መጋቢነት ነው ።

እሱ ዘወትር ፍጥረትን ስለሚያስብ በዓውደ ፀሐይ ዕለታትና ዓመታትን በማፈራረቅ ለፍጥረቱ በተለይም ለሰው ልጅ አዲስ ዘመንን ይመግባል ፡ እሱ ፍጥረቱን ስለሚያስብ ክረምትን ለዘር ፡ በጋን ለመከር ፡ መዓልትን ለሥራ ሥምሪት ሌሊትን ለዕረፍት በማዘጋጀት ፡ የዝናሙን ርዕደት ፡ የፀሐዩን ሙቀት ፡ የነፋሱን ግፊት ለመኖር በሚያስችል ሁኔታ በመመጠን ሁላችንንም ከዕለት ወደ ዕለት ከዓመት ወደ ዓመት እንድንሸጋገር ያደርጋል ።

አሁንም ነቢዩ ዳዊት በመዝሙሩ ትፌኑ መንፈስከ ወይትፈጠሩ ፡ ወትሔድስ ገጸ ለምድር መንፈስህን ትልካለህ ይፈጠራሉም ፡ የምድርንም ፊት ታድሳለህ



ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ የቅዱስ ሲኖዶስ ሰብሳቢ ሊቀ ጳጳስ ቃለ ቡራኬ ሲያስተላልፉ

ሲል እንደተናገረው ምንጊዜም ለፍጥረት የሚያስብ አምላክ በየዓመቱ አዲስ በሚፈጠር ልምላሜና ጽጌ የሕይዋን ሁሉ መኖሪያ የሆነችውን ምድር ፊት በማድመቅ ወይም በማደስ እኛ በደስታ እንድንኖር ያደርጋል ።

ስለዚህ እኛ ሕያዋን እግዚአብሔርን በየሰዓቱ ፡ በየዕለቱና በየዓመቱ እናመሰግነዋለን ፡ ልናመሰግነውም ይገባል ። ስለኑሮ ክነሳን ዘንድ ቅዱስ መጽሐፍ ሰው በእንጀራ ብቻ ለመኖር እንደማይችል የተናገረውን ቃል ማሰብ ያስፈልጋል ። የእግዚአብሔር ረድኤት ከሰው ልጆች ከራቀ ሰው ከእህልና ውኃ ብቻ የሚፈልገውን ዓይነት የደስታና የሰላም ኑሮ መኖር ስለሚሳነው ወደ ማይፈልገው ጭንቀት ውስጥ መግባት ዕድል ፈንታው ይሆናል።

ነቢዩ ሙሴ "ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው ነገር ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ በሕይወት እንደማይኖር ያስታውቅህ ዘንድ ሊያስጨንቅህ" ሲል በእግዚአብሔር ቁጣ ለተጨነቀው ሕዝበ እሥራኤል የጭንቀቱን ምክንያት የገለጸውና በኋላም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰይጣን ሊፈታተነው ለመጣው ሰይጣን ይህኑ ቃል ደግሞ የተናገረውም ስለዚህ ነው። የሕይወት ኑሮ ማለትም ፍቅርና ሰላም ፡ አንድነትና ኅብረት ፡ ደስታና ብልጽግና የሰፈነበት ዓይነት ኑሮ ማለት ነው ። ይህ ዓይነቱ የሕይወት ኑሮ በእርግጥ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ጸጋ ስለሆነ የሕይወት ጌታ እግዚአብሔር ምንጊዜም ይህን ጸጋ እንዳይነሣን ሁነን መገኘት ይገባናል ።

የሰላም አምላክ ከዚህ ዕለትና ሰዓት እንዳደረሰን ለሚመጣውም ዓመት በደኅና አድርሶ ስሙን ለማመስገን ያብቃን ።

በዓሉን የደስታና የሰላም በዓል ያድርግልን ።

የሰላም አምላክ ለሀገራችን ሰላምንና ብልጽግናን ይስጥልን ።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ለዘለዓለም ይባርክ ።

# አዲስ ዘመን

አዲስ ማለት ስሙ እንደሚያመለክተው በአዳዲስ ነገሮች የማይደሰትና እሮሮው የማይታደስ ሰው የለም አዲስ አዲስ ነውና ፡

አሮጌው ዘመን አልፎ አዲሱ ዘመን ሲተካ የሰው ልጆች በጉጉት ነው የሚቀበሉት በጉጉት መቀበላቸውም ያለምክንያት አይደለም አብዛኛውን ጊዜ አዲስ ልብስ አዲስ ጫማ የሚገዛው የዚሁ አዲስ ዘመን ተንተርሶ ከመሆኑም ሌላ ጉመን ሲጨምቅ የከረመውም ሁሉ አዲሱን እህል የሚቀምስበት ከችግሩ የሚላቀቅበት ጊዜ በመሆኑ ነው ።

ከዚህ የተነሣ ገንዘብ ያለው ደስ የሚለውን አዲስ ልብስን ገዝቶ ለብሶና አጊጦ ሲውል ገንዘብ የሌለው ደግሞ ዓቅሙ በሚፈቅድለት መጠን በቀላል ዋጋ ገዝቶ ያም ባይሆን አሮጌውን ጨርቅ በሳሙናና በውኃ አጥቦ አዲሱን ዘመን በደስታ ይቀበለዋል ።

አዎ አዲሱም ዘመን ይዞዋቸው የሚመጣዉ ብዙ የሚያስደስቱ ነገሮች አሉ እነዚህም ፩ኛ መሬቱና ሰማዩ በደመና ተሸፍነው ከከረሙ በኋላ በዚህ በአዲሱ ዘመን መሬቱን ሸፍኖት የከረመው ጉም ተገፎ መሬትዋ የተለያዩ አዝርእትንና አረንጓዴን ለብሳ በተለያዩ ፍራፍሬዎችም አጊጣ ስትታይ በዚህ አንጻር ደግሞ በጥቁር ደመና ተሸፍና የከረመው ሰማይ ደመናው ተወግዶለት ብርሃን በሆኑ ከዋክብት አሸብርቆ የሚታይበት ጊዜ ነው።

፪ኛም ወንዞች ሞልተው ዘመድ ከዘመዱ ጋር እንዳይገናኝ አጥር ሁኖ ከከረመ በኋላ በዚህ ዘመን በናፍቆት ከርመው ፊት ለፊት እየተገናኙ ሰላምታ የሚለዋወጡበትና የሚጠያየቁበትም ሰዓት በዚህ በአዲሱ ዘመን መሆኑ ከሁላችን የተሠወረ አይደለም ።

ስለዚህ ተለያይተው የከረሙት ሁሉ እንኳን ለአዲሱ ዘመን ለመሸጋገር አበቃችሁ እያሉ መንፈሳዊ ሰላምታ የሚለዋወጡበት ልባዊ ደስታቸውን የሚገልጹበት በመሆኑ ነው እነዚህን ሁሉ አዲስ ዘመን ይዘዋቸው የሚመጡ ናቸው ።

ይህ ብቻ አይደለም በየመንገዱ በዓይናችን የምናየው በጆሮቻችን የምንሰማው እንኳን ለአዲስ ዘመን አደረሰህ ለሚመጣውም በሰላም ጠብቆ እንዲያቆየን እንመኛለን የሚለው አስደሳች ዜና ነው ሲናፈስ የምንሰማው ። ከሀገር ውጭ ያሉትም ዘመዶችና ቤተ ሰቦች ይህንን አዲስ ዘመን ምክንያት በማድረግ በካርድ በልዩ ልዩም ደብዳቤዎች ምኞታቸውን እየጻፉ ይገልጻሉ እነዚህን ሁሉ አዲስ ዘመን ይዝዋቸው የሚመጡ ናቸው ።

ይሁን እንጂ አዲሱ ዘመን ሲመጣ የምናስተውላቸው የምንመረምራቸው ብዙ ጉዳዮች እንዳሉ መርሳት የለብንም ። ይኸውም እንደኛ ያለፈው አሮጌ ዘመን ሠርተንበት ከሆነ በሠራነው ሥራ እየተደሰትን እንደገና በዚሁ በአዲሱ ዘመን የበለጠውን ሥራ እንድንሠራ ያስፈልጋል ። ባለፈው አሮጌ ዘመን ያልሠራንበት ከሆነ ግን ባለመሥራታችን እየተጸጸትንና እያዘንን ባጭር ታጥቀን እንድንሠራበት ነው ፡

እንደሚታወቀው ዘመኑን አዲስ የሚያደርገው ሰው ነው አሮጌ የሚያደርገውም ሰው ነው ለማለት ይቻላል ።

ምክንያቱም አንድ ሰው በኑሮው ሁሉ ለውጥ ካላገኘና ካልተሻሻለ ወደ አዲስ ዘመን ቢደርስም ያው አሮጌ እንጂ አዲሱ ዘመን አዲስ ሊሆንለት አይችልም ። አዲሱ ዘመን አዲስ ሊሆንና የአዲስነቱን ትርጉም ሊያገኝ የሚችለው ተሐድሶ አግኝቶ ሲገኝ ነው።

ዛፎችን እንኳን በበጋ ስንመለከታቸውና በዚህ በአዲስ ዘመን ስንመለከታቸው የተለያዩ ሁነው እናገኛቸዋለን ። የበጋ ዛፎች ቅጠላቸው ጠውልጎ አበባቸው ረግፎ ቅርንጫፎቻቸው ደርቀው በጠቅላላ የልምላሜያቸው ሥነ ባሕርይ ተለውጦ ነው የሚታየው ።

በአዲሱ ዘመን ግን ዛፎቹ ልምላሜያቸውን ለብሰው ብዙ ሕብረ መልክ ባላቸውም አበባዎች አሸብርቀው ነው የሚታዩት እንዲህ





www.ethiopianorthodox.org

ከሆነ ከእኛ የሚፈለገውና ከእኛ የሚጠበቀው እንኳን አዲስ ዘመን መጣልን የሚለው አነጋገር ብቻ ሳይሆን በዚህ በአዲስ ዘመን አዲስ ሰው አዲሱን ሥራ መሥራት አዲሱን ዓላማ መቀየስ ነው ፡ አዲሱን ዘመን መመኘት አዲሱን ሥራ ለመሥራት መሆን ይኖርበታል። ሰው ካልሠራ ተሐድሶ አያገኝም ተሐድሶም ካላገኘ አይሻሻልም ። የውጭ ሀገር ሰዎች በሰማይ የሚበሩ በባሕር የሚንሳፈፉ በየብስም የሚሽከረከሩ የተለያዩትን ጥበባት አስፋፍተው የሚታዩት ሠርተው በመገኘታቸው ነው እንግዲህ እኛም ቢሆን እንደ እነሱ ለመሆን የምንበቃው እንደ እነሱ ሠርተን ስንገኝና አሮጌውን ዘመን በሥራ ስንተረጉመው ነው እንጂ አዲስ ዘመን የሚለው ቃል በሥራ ካልተተረጐመ ያው ተመልሶ አሮጌ መሆኑ ነው ።

በተለይ ይህንን ፲፱፻፹፬ ዓ.ም. ከዚህ በፊት ከነበሩት ዘመናት ከፍ አድርገን ማክበር ይገባናል ምክንያቱም የሰው መብትና ሰብአዊ ክብሩ የተጠበቀበት ዲሞክራሲ የፈለገውን እንዲጽፍ እንዲናገር የተደረገበት ጊዜ በመሆኑ በበለጠ ማክበር ይገባናል ። በዚህ በሽግግር ገዜ የበለጠ የሥራ ድርሻ ይጠበቅብናል ። ባለፉት ፲፯ ዓመታት አዲሱን ዘመን ስናከብረው የቆየነው በውድ ሳይሆን በግድ ከቤታችን እየወጣን በአብዮት አደባባይ ነው ስናከብረው የቆየነው በአሁኑ አዲስ ዘመንና በዚህ በ፲፱፻፹፬ ዓ.ም. ግን የሰላምና የመረጋጋት የዲሞክራሲ ጊዜ ለማየት ስላበቃን አምላካችን እየመሰገንን በበለጠ ማክበር ግዴታችን ነው እጽፍ ድርብም ደስታ ሊሰማን ይገባል ።

የተፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ባለበት ጸንቶ የማይኖር ተለዋዋጭ ነው ከመለዋወጡም አልፎ ጨርሶ እንደ ሚጠፋና እንደሚያልፍ ጽሑፎች ያስረዳሉ ። አዲስ ያረጃል አሮጌ የነበረውም ይታደሳል በበጋ ደርቆና ጠውልጎ የባጀው በወርኀ ክረምት አዲሱን አካል ይዞ ይነሣል አሮጌውም ሁሉ ይታደሳል ። ይህንን ኃይለ ቃል በማስመልከት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ሁሉም አዲስ ፍጥረት ነው አሮጌው ነገር አልፎ አል እነሆ ሁሉም አዲስ ሁኖአል ብሏል ፪ኛ ቆሮ ፭ ፡ ፲፯ ።

ሐዋርያው እንደገለጸው አሮጌው ዘመን በማለፉ እነሆ አዲሱን ዘመን ጀምረነው እንገኛለን ታድያ በዚህ በአዲሱ ዘመን በአዲስ መንፈስ ተነሥተን ባጭር ታጥቀን የማስተማር ሥራችንን መከሄድና በሚገባ ማከናወን ትምህርተ ወንጌልንም ላልደረሳቸው ሰዎች በተቀላጠፈ ሁኔታ ማድረስና የተረሱትን ወገኖቻችንን ማውሳት ይጠበቅብናል ። የዚህ ዓይነቱ ሥራ አማራጭ የሌለው መንፈሳዊ ሥራ እንደመሆኑ ይህንን አዲስ ዘመን በአዲስ ሥራ እንተርጉመው ።

ከንፈ ርግብ ማርቆስ

# ለአ.... ማር አይጥመውም

## ካለፈው የቀጠለ — ቁጥር ፩፻፺

ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን ቃል (ቃለ ካህን) ስለሆነ የካህኑን ቃል ለማክበር ሲል መጽሐፍ ቅዱሱን ይዞ ወደ መድረኩ ሲወጣ ቃለ ወንጌል ትምህርተ ወንጌል መስማት የተሰበሰበው አዛውንቱ አሮጊቱ ወጣቱ ኮረዳዪቱ ሁሉ ዓይኑን ወደ አስተማሪው ተክሎ ይመለከተው ጀመር አንዳንዱ አሁን ምን ብሎ ሊሰብክ ወይም ሊናገር ነው ከመድረኩ ላይ የወጣው ? ሲል እኩሉ ደግሞ ሲገርመው የሚያናግረው ሰው እንዳለ ሁሉ በልቡ እየታዘበ ዓይኑን አፍጦ ዝም ብሎ ይመለከተው ጀመር መምህሩም (አስተማሪውም) በሕዝቡ አእምሮ ያለውንና የሚጉላላውን መጠይቃዊ ሀሳብ ተረድቶታልና መጽሐፍ ቅዱሱን ከመክፈቱ ማለት በአትሮንሱ አስቀምጦ ከመግለጡ አስቀድሞ ምእመናን ሆይ ወደ ትምህርቱ ከመግባቱ በፊት አንድ የምናገረው ትምህርታዊ ምሳሌ ስላለኝ በጥሞና እንድታዳምጡኝ በትሕትና እጠይቃለሁ ሲል ሕዝቡ ደግሞ ምን ሊናገር ነው ብሎ ሁሉም ዕዝነ ልቡናውን ከፍቶ በጉጉት ይጠባበቀው ጀመር ።

አስተማሪው ከዚህ አከታትሎ አንድ ባለጸጋ ሰው በቤቱ ብዙ የማር ወለላ ነበረው አለ ቀጠለና ይህ ሰው አንድ ቀን ሁለመናዋ በቁስል በተመታች ገጣባ አህያ ማሩን በስልቻ ጭኖ ወደገበያ ይዞ ወጣ እገበያ እንደደረሰም ለካስ ስልቻው ቀዳዳ ኖሮ የማር ወለላው በቀዳዳው ስልቻ እያፈተለከ በአህያይቱ ቁስል አድርጎ ወደምድር የሚወርደውን የማር ወለላ በእጅ እየጠረገና እያንቋረረ እየተሻማ ይልስ ነበር እንጂ የአህያይቱ ቁስል አላስጠላውም አልቀፈፈውም ነበር አለ ።

ተናጋሪው ከዚህ በላይ ያለውን ኃይለ ቃል ተናግሮ ዓይኖቹን ወደ ሕዝቡ ተክሎ ለጥቂት ደቂቃዎች ዝም አለ በትምህርተ ወንጌሉ አዳራሽ ባሉት ሁሉም ዝምታ ሰፈነ



አስተማሪው ንግግሩን በመቀጠል አብዛኞዎቻችሁ አሁን የተናገርሁት ምሳሌ የገባችሁ ይመስለኛል "ያልገባችሁ እንዳላችሁ ግን እንዳብራራላችሁ ትፈቅዱልኝ ዘንድ በትሕትና እጠይቃለሁ ካለ በኋላ የሁሉም ባለቤት እግዚአብሔር ነው የማር ወለላ ምሳሌ የእግዚአብሔር ቃል ነው ገጣባይቱ አህያ የኔ ምሳሌ ናት ስለዚህ አሁን እኔ በእናንተ ፊት የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተማር ስነሣ ሁላችሁም በኔ ላይ ያለውን ኃጢአት ስለማታውቁት ምን ብሎ ሊያስተምረን ነው ? ብላችሁ እንዳሰባችሁ ይሰማኛል ነገሩ እውነት ነው እኔ እጅግ ጥፋተኛና ኃጢአተኛ መሆኔን ከእናንተ ይልቅ እኔ ራሴ አውቀዋለሁ ከኔ ይልቅ ደግሞ እግዚአብሔር እንዴት ነጥብ ሳትወድቅ የሠራሁትን ኃጢአት ሁሉ መዝግቦ እንዳስቀመጠው አምናለሁ ነገር ግን እኔ የምናገረው የእግዚአብሔርን ቃል እንጂ እናንተን አይመለከትም ከኔ ላይ የምትመለከቱት ኃጢአት የሚያጠፋኝ ወይም የሚያስቀጣኝ እኔን እንጂ እናንተን አይመለከትም ከኔ ላይ የምትመለከቱት ኃጢአት የምትነበብ ጥፋት ሁሉ ማንንም አይጐዳም ይልቅስ ከእኔ ሳይሆን እግዚአብሔር በእኔ አማካይነት የሚያስፈልጋችሁን ከማር ወለላ የበለጠ የሚጣፍጠውን የእግዚአብሔርን ቃል እየላሳችሁ የሥጋችሁን ቁስል መድኃኒት ተቀበሉ እግዚአብሔር መንፈሳዊ ምግብ አጥተው በነፍሳችው የተራቡትን በቅዱስ ቃሉ የሚያጠግብ ሕያውና ዘለዓለማዊ አምላክ ነውና ትምህርታቱን አዳምጡ ብሎ ከዚሁ ጋር የሚዛመድ ክፍል ከቅዱስ ወንጌል አውጥቶ ቢያስተምራቸው ሕዝቦቹ ከስሕተታቸውና ከመጥፎ አመለካከታቸው በአንብአንስሐ ተመልሰው ትምህርቱን በጥሞና ተከታትለው ምግበ ነፍስን ይዘው በደስታ ወደ ቤታቸው ተመልሰው ይባላል ።

ማንኛውም ሰው እምነቱ የቱን ያህል ጥልቀት እንዳለው ከእምላክ በስተቀር ሌላ ፍጡር እንደማያውቀው ቢታመንም በዘመናችን እንደሚታየው ዕገሌ እምነቱ ከዕገሌ ይበልጣል ብሎ የማበላለጫ ደረጃ የሚሰጠው ያለ አይመስለኝም ምክንያቱም በክርስቶስ ስም ሐሰተኞች መምህራን በሰዎች ልብ ኑፋቄ በመዝራታቸው ጦርነት በዓለም ላይ በመስፋፋቱ ሰውና ሰው በመፋጀቱ ፡ ፍቅር ከሰዎች መካከል ፈጽሞ በመጥፋቱ ፡ ድንጋጤን ፈጥሮአል ። ራብም ቸነፈርም የምድር መናወጥም በልዩ ልዩ ሥፍራ በመከሠቱ ሰዎች የሚያዙትንና የሚጨብጡትን አጥተዋል ። እነዚህ ሁሉ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመሠረታት ሐዋርያት ያስፋፉአት ሠለስቱ ምዕት ሥርዓትና ደንብ የደነገጉላትና ነገረ መለኮትን ያብራሩላት ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን እየተዉ ሌላ እምነት በመከተላቸው ነው ።

አንዳንዶችም ቅብዝብዛሞችና ቅዝታሞች ሆነው መታየት ጀምረዋል ታድያ እንደነዚህ ያሉ ቀላዋጮች ሁሉ ማር የማይጥማቸው ከንቱዎች ናቸው ተብለው ይጠራሉና ከነዚህ ተጠንቀቁ እንላለን። ቀላዋጮች ከዚህም ከዚያም ሳይሆኑ ይጠፋሉ ቀላዋጭ ሰው ከቤቱ ጣፋጭ ምግብ መጠጥና አስፈላጊ የሆነ ነገር ሁሉ እያለ ወደሌላ ሰው ቤትና ወደ አልባሌ ሥፍራ ሄዶ መናኛ መብልና መጠጥ መብላትና መጠጣት ደስ ያሰኘዋል ከቤቱ ያለች የልጆቹን እናት የሕግ ሚስቱን ያስንቀዋል የቤቱን ያማረ የሠመረ ምግብ ያስጠላዋል" ከውጭ ሰክሮ አመንዝሮ እየተወላገደ እየወደቀ እየተነሣ እየለፈለፈ ሀብቱን ንብረቱን አጥፍቶ ተንቆ ተጠልቶ ይመጣል ። በመጨረሻ ግን የቀላዋጭ ነገር ውርደትና ሞት ነውና ልቡ በመጠጥ ኃይል ፈንድቶ ወይም በወሮበሎች ተመትቶ አይጠፉ ጠፍቶ የትም እንደሚቀር የታመነ ነው ።

እምነታቸውን ሃይማኖታቸውን (ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናቸውን የሚንቁ ሥነጽሑፎችዋንና መምህራኖችዋን ሊቃውንቶችዋንና ሥርዓቷን የሚያቃልሉ የሚጠሉ ሁሉም አጠፋፋቸው እንደቀላዋጮቹ ነው በየቤተ ክርስቲያኑ የሚሰጠው ትምህርተ ወንጌል በጋዜጣው በመጽሔቱና በመጻሕፍቱ የሚጻፈውና የተጻፈው ቃለ እግዚአብሔር አይጥምም አይጣፍጥም እያሉ የሐሰተኞች ባሕታውያን ባዮች በተሰበከ ስብከት የሚማረኩ ቀላዋጮች እንደ አመንዝራ ልባቸው ወደገደል ይዞአቸው ይገባል ። ምክንያቱም እንደማር የሚጥመውን ትምህርተ ወንጌልና መታንን የሚያነሡ የሥነ ጽሑፎቻችን ጣዕምና ለዛ ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት እያለላቸው ጥለው ፈርጥጠዋልና ነው።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባስተማረበት ዘመን በምገስ ቃሉ በሳዕማን አፉሁ" ከማር ወለላ መቶ እጅ በሚጣፍጠው አንደበቱ ቢያስተምር ተማርከው አምስት ገቢያ ያህሉ ሰዎች ይከተሉት እንደነበር የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይነግረ



www.ethiopianorthodox.org

ናል ለነዚህም ሁሉ በአምስት የገብስ እንጀራና በሁለት ዓሣ ምግብ አጥግቦ ትርፍራፊው አሥራ ሁለት ቅርጫት ሙሉ አሥነሥቶአል ። እነዚህ ሰዎች የጌታችን ኃይለ ተአምራት አይተዋል አድንቀዋል ። ነገር ግን ያላዩትን ሌላ ተአምራት እንደገና ለማየት በየዕለቱ ሳይጥሩ ሳይግሩ በተአምራት ምድራዊ እንጀራ በመብላት በሥጋዊ ሕይወት ለመኖር መፈለጋቸውን ተረድቶ እናንተ አሁን እኔን የምትፈልጉኝ እንጀራን ስለበላችሁና ስለጠገባችሁ ነው እንጂ ምልክቶችን ስላያችሁ አይደለም” ሲል ከልብ እንዳልተከተሉት አውቆ ወደየመጡበት ዓለማዊ ኑሮአቸው አሰናብቶአቸዋል ።


እነማር አይጥመው የዘመኑ ቀላቀሎችም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃያማኖት በእመቤታችን በመላእክት በሰማዕታት በጻድቃን በሐዋርያት የምታሳየውን የሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን አስደናቂ ተአምር እያዩ እንደገና እንዳላዩ ሆነው በአምላካዊ ሥራውና በቃሉ መፈታተን ልማዳቸው ነውና ቤ/ ክርስቲያናችንን እንኪያ ዓይተን እንድናምንሽ አንቺ ምን ምልክት ታደርጊያለሽ ምንስ ትሠሪያለሽ እያሉ ከሰማይም ይሁን ከምድር ሥጋዊ እንጀራ ታዘንምላቸው ዘንድ ጠይቀዋት ሰማያዊ ምግብ እንጅ ምድራዊ ምግብ የለኝም ብትላቸው ሻይ ባኒ፣ ሐራጅና ሰልባጅ ልብስ ወደሚቀላውጡበት እየሄዱ አንድ እሁድ ወደ ርሱ በሳምንቱ እሁድ ወደኛ እየመጡ ምእመናኖቻችንን የሚበጠብጡ እነ ማር አይጥመው ሳይጋለጡ በሄዱበት ጠማማ ጉዳና አርፈው ይቀመጡ እንላለን ።

ሊ/ ትጉ ገብረ ክርስቶስ ኃ/ማርያም

## ዜና ሊቃውንት

# የመሪጌታ ልሳነወርቅ ገብረ ጊዮርጊስ ገብረ ሥላሴ የሕይወት ታሪክ

መሪጌታ ልሳነ ወርቅ ገብረ ጊዮርጊስ በትግራይ ክፍለ ሀገር በእንደርታ አውራጃ በታታ ወረዳ በማየ እንበሳ ገዳም ከአባታቸው አቶ ገብረ ጊዮርጊስ ከእናታቸው ወይዘሮ ምጽላል በ፲፱፻፴፩ ዓ.ም. መጋቢት ፲፪ ቀን ተወለዱ ።



መሪጌታ ልሣነ ወርቅ ገ/ጊዮርጊስ እኒህ ናቸው

በሥርዓተ ሕፃናት በምክርና በእንክብካቤ አድገው በ፮ ዓመታቸው ከአባታቸው ታላቅ ከመምህር ተድላ ፊደል ቆጥረው ሐዲሳት መጻሕፍትንና መዝሙረ ዳዊትን አንብበው አጥንተው እንደፈጸሙ በዚያው በአጠገባቸው ከነበሩ የታወቁ ስመ ጥሩ የሰለልኩላ መዝገበ ቅዳሴ መምህር የኔታ ሀብተ ሥላሴ ዘንድ ገብተው መዝገበ ቅዳሴ አጠናቀው ተምረው በመምህርነት ተመረቁ ።

ነገር ግን ሕፃን ስለነበሩ በመምህሩ ፈቃድ አባታቸው በ፲፱፻፵ ዓ.ም መጋቢት ወር ጨሌቆት ሥላሴ ወስደው ድጓ እንዲማሩ ለድጓውና በ፵፬ቱ ጉንደር አቋቋም መምህርነት ለታወቁት ዋናሊቅ ለመምህር ቀለመወርቅ ፍትዊ ሰጡአቸው ።

መሪጌታ ልሳነ ወርቅም ውዳሴ ማርያም ዜማ ጀምረው ቀንና ማታ ቃል ትምህርት ተምረው እንደፈጸሙ ጾመ ድጓ ገብተው ቀን ጾመ ድጓ ማታ ምዕራፍ እየተማሩ አጥንተው እንደ ፈጸሙ በ፵፪ መስከረም ፳ ቀን ድጓ ጀምረው ፪ ጊዜ ዘልቀው በ፵፰ ዓ.ም በመምህራቸው ፈቃድ ቅኔ ሊማሩ ከመምህር አብርሃ ዓለም አየሁ ዘንድ ገብተው ቅኔንና ዝማሬ መዋሥእት ተምረው መልሰው ድጓውን ሊከልሱ ወደ የኔታ መምህር ቀለመወርቅ ጨሌቆት ወርደው ድጓውንና ምዕራፉን በሚገባ ከልሰው አበጥረው አውቀው አቋቋሙንም ተምረው በ፲፱፻፶፰ ዓ.ም ድጓ እንዲያስተምሩ ፈቅደውላቸው ከሐምሌ ወር ፶፰–፶፱ ዓ.ም ኅዳር ወር በመምህራቸው ፊት ሁነው ድጓ ሲያስተምሩ ቆይተው እንደገና ድጓ እንዲያስመሰክሩ በመምህራቸው በመምህር ቀለመወርቅ ተመርቀው ከጨሌቆት ሥላሴ ታኅሣሥ ፩ ቀን ፲፱፻፶፱ ዓ.ም ተነሥተው ጥር ፯ ቀን ፶፱ ዓ.ም ከድጓው ምስክር ቤተልሔም ገቡ ዋናውን ምስክር መጽሐፈ ጥበብ የተባለውን ድጓ እየቃኙ ከድጓው ምስክር ከመምህር አምሳሉ መርሻ ፊት ሰተት አድርገው በአድናቆት ሚያዝያ ፴ ቀን ፶፱ ዓ.ም በመዝለቃቸው ድጓ ምስክር ሁነው በእግራቸው እንዲተኩ መረቋቸውና መሪጌታ ልሳነ ወርቅ ብለው የመምህርነት መዓርግ ሰጡአቸው ።

መሪጌታም በትምህርት ቤቱ ድጓ እያስተማሩ ምዕራፍ እየጻፉ ከርመው ቀጥለው ጾመ ድጓ ጽፈው በኅዳር ወር ፲፱፻፷ ዓ.ም ዝማሬ ሊያስመሰክሩ በመምህራቸው ፈቃድ ዙር አምባ ወጥተው ከዝማሬው ምስክር ከመምህር መራሒ ወልደ ጊዮርጊስ ዝማሬ መዋሥዕት አስመስክረው የድጓ ብራና አውጥተው እንደገና ድጓ ሊጽፉ ቤተ ልሔም ወርደው በመምህር አምሳሉ ፈቃድ በቤተ ክርስቲያኑ ያሉ ድጓዎች መጽሐፈ አእምሮና መጽሐፈ ጥበብ ብርሃን ዓለም ተሰጥቶዋቸው በጥንታቄ ተመልሰና ፍቀሽ ሳይኖረው ድጓቸውን ጽፈው አሳምረው ተመስገን ነው ምስክሩ በእኔ እግር ይተካሉ ብለው ሲጠብቁአቸው መሪጌታ ልሳነ ወርቅ ገብረ ጊዮርጊስ ሀገሬን እገባለሁ እንጂ እንደጨሌቆቹ አልቀርም ብለው ስለ ለመኑአቸው በመሄዳቸው መምህር አምሳሉ እያዘኑ የድጓ ምስክርነታቸውን ጽፈው አትመው ሰጥተው መርቀው በግንቦት ወር ፲፱፻፷፪ ዓ.ም አሰናበቱአቸው ። መሪጌታ ልሳነ ወርቅም ከዚያ ወጥተው በጐንደር አካባቢ ኖራ ኢየሱስ በተባለ ደብር ድጓ ሲያስተምሩ ከርመው የካቲት ፯ ቀን ፲፱፻፷፫ ዓ.ም ሀገራቸው ገብተው ደብረ ኃይለ ማርያም በተባለ ገዳም ተመድበው ድጓ ሲያስተምሩ ድጓውንና ጾመድጓውን በቴፕ ሪከርድ እንዲቀርፁ በንጉሥ ኃይለ ሥላሴ ትእዛዝ ታህሣሥ ፬ ቀን ፲፱፻፷፮ ዓ.ም ተጠርተው አዲስ አበባ መጡ ከብዙ ድጓ መምህራን በፊተና አንደኛ ወጥተው በንጉሡና በአቡነ ባስልዮስ መልካም ፈቃድ በማስታወቂያ ሚኒስቴር ውስጥ ከታኅሣሥ ፯ ሚያዝያ ፴/፷፮ ዓ.ም በትጋትና በጥንቃቄ ድጓውን በድምፃቸው እያስማሙ በቴፕ ሪከርድ ቀርጸው በመፈጸማቸው በሥራው አስፈጻሚ ክቡር አቶ አበበ ረታ አቅራቢነት ከንጉሥ ኃይለ ሥላሴ ፊት ቀርበው ለሊቃውንት የሚገባ የአንደኛ ከፍተኛ መዓርግ ሙሉ ወርቅ ካባ ከነ ወርቅ ቱፍ ባኑ ተሸልመዋል

ከዚያ ወደ ትውል ሀገራቸው ተመልሰው ድጓ ሊያስተምሩ በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም በሥርዓተ ተክሊል በዲቁና መዓርግ ተዳሩ ። መልሰው በኅዳር ወር ፲፱፻፷፱ ዓ.ም መቀሌ ተዛውረው በአፄ ዮሐንስ ቤተ መንግሥት የተቋቋመው የኢትዮጵያ ጥንታዊ ታሪክና ቅርስ ዋና ጸሐፊ ሁነው እስከ ፲፱፻፸፫ ዓ.ም ፶፩ የታሪክ መጻሕፍት በቁም ጽሕፈት ጽፈውና አንዳንዱንም በአማርኛ ተርጉመው አበርክተዋል ።

በዚህ ሁሉ ሞያቸውና ሥራቸው ዝናቸው በሁሉ ስለታወቁ የባህል ሚኒስቴር ግንቦት ፲፱ ቀን ፲፱፻፸፫ ዓ.ም. ከመቀሌ ወደ አዲስ አበባ አዛውሮ ከነቤተሰባቸው አምጥቶ የቅዱስ ያሬድን ጸዋት ዋዜማ በሙሉ ከነታሪኩ እንዲያስተምሩ በያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤት መድቦአቸው እስከ ዛሬ ፲፱፻፹፬ ዓ.ም በትጋት ሲያስተምሩ በትርፍ ሰዓታቸው አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ እየተመላለሱ በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ውስጥ ብዙ የታሪክ መጻሕፍትን እየመረመሩ መልካም ታሪኮችና በማዕዶት መጽሔትና በትንሣኤ ከማስተላለፋቸው ሌላ (የቅዱስ ያሬድን ትክክለኛ ታሪኩን ከነዜማው በጥሩ ድምፃቸው እያሣመሩ በዓለም ዓቀፍ ሬድዮ ለመላ ዓለም ባሰሙ ጊዜ ዓለም ሁሉ አድንቆታል ።

ይሁን እንጂ መሪጌታ ልሳነ ወርቅ ገብረ ጊዮርጊስ እንደሞያቸው ጥራት እንደ አገልግሎታቸው ብዛት ተመጣጣኝ ደረጃ ሳይሰጣቸው ዓሥር ቤተ ሰብ ይዘው በተመደቡበት ቦታ በማስተማር ሥራቸው ተገኝተው ሲያስተምሩና ብዙ ታሪክ ሊመረምሩና ሲጽፉ ይገኛሉ ። ከዚህም ሌላ ማናቸውንም የታሪክ አመጣጥና ልዩ ልዩ ተፈላጊ የሆኑትን ጥያቄዎች ለሚጠይቅ ሰው ከነማስረጃው ከመቅጸበት አጥጋቢ መልስ ሲሰጡ እጅግ ያስደስታሉ ስለዚህ እንዲህ ላሉትና መተኪያ ለሌላቸው ሊቅ በደከሙበት ሙያ ተሰማርተው ቢያስተምሩ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ብዙ መምህራን እንደሚያስገኙ ጥርጥር የለውም ። ከላይ በተገለጸው መሠረት ተገቢ ትኩረት ተደርጎ የሚመለከተው ቢያስብበት መልካም ነው እንላለን ።

አቅራቢ ቀኝ ጌታ ጥዑመልሳን ከበደ



www.ethiopianorthodox.org

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ተሐድሶ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ፡

ለአንዷት ቤተ ክርስቲያን ከማንኛውም ነገር ሁሉ አስቀድሞ የአስተዳደር ተሐድሶና መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ጠንካራ ሲኖዶስም ያስፈልጋታል ። ይህ ካልሆነ በየጊዜው ከሚነሳው ትውልድ ጋር አብራ ለመሄድና እራሷ ተንቀሳቅሳ ሌላውንም ልታንቀሳቅስ አትችልም መሻሻል መታደስ በየጊዜውም ለውጥ ማድረግና መንቀሳቀስ እንኳንስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን ይቅርና የአንድ ግለሰብ መኖሪያ ቤትና አስተዳደር እንኳ የኑሮ መሻሻል የአስተዳደር ለውጥ ካላገኘ እራሱንም ቤተሰቡንም ይበድላል ።

እስካሁን ድረስ ቤተ ክርስቲያኗ የቆየችው መሻሻልና መለወጥ እምነትን የሚነካ እየመሰላት እንደ ኩሬ ውሃ በአንድ ቦታ ቆማ በአብርሃና አጽብሐ ዘመነ መንግሥትና በአቡነ ሰላማ መጀመሪያ በተመሠረተው አመራር ከመሄድ በቀር በውስጧ የሚተዳደሩት ሊቃውንትና ምእመናን እነሱ ተሻሽለው ሌላውም እንዲሻሻል ሳታደርግ ባለህበት እርገጥ በሚለው ባልሆነ ፈሊጥ እየተመራች እስካለንበት ጊዜ ድረስ ቆይታለች ስለዚህ ሃይማኖትን ከሚመለከቱ ነገሮች በስተቀር ጊዜውን ተከትሎ መሻሻልና ለውጥ እንደሚያስፈልግ ተሐድሶም እንደሚያሻ ከኦሬንታል አብያተ ክርስቲያናት መረዳት ያስፈልጋል ።

በአለፈው ዘመን ከተፈጸሙት የአስተዳደር ሥራዎች መካከል ጥቂቶቹን ብንጠቅስ ፩ኛ እንደሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት እራሷ የአስተዳደሩን አመራር መፈጸም ሲገባት በመንግሥት ጥላ ስር ሆና በየጊዜው ለሚነግሡት ለኢትዮጵያ ነገሥታት እንድትታዘዝና ለእነሱ ሰፋ ያለውን አገልግሎት እንድትፈጽም ፤

፪/ ከሊቃውንቶቿ የአድባራትና የገዳማት አበምኔት የሚሆኑትን መነኮሳት እሷ መሾም ሲገባት ከመንግሥት ዘንድ አቅርቦ ማሾም የሚሻሩትንም ማሻር ነበር ይህንንም በማድረጓ ድክመትን እንጂ እድገትን አላስገኘላትም በይበልጥም በወደቀው በደርግ መንግሥት አያሌ ግፎች ተፈጽመውባታል እነዚህም ፡

ሀ· መስሎቹን በላይዋ ላይ እየሾመ የቅድስት ሥላሴና የታእካ ነገሥት በዓታ የመግቢያ በሮችን በመዝጋትና ትምህርት ቤትንም በመውረስ ፡

ለ· በቤተ ክርስቲያን በድምፅ ማጉያ እንዳይሰበክና ምእመናኑ ተበሳጭተው ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዳይመጡ በማድረግ ፡

ሐ· የቤተ ክህነት ሠራተኛ በይግባኝ መብቱ እንዳይጠቀም በየፍርድ ቤቶቹ የእገዳ ጽሑፍ በማስተላለፍ ፡

መ· ፓትርያርኩን ጳጳሳትን እና መነኮሳትን ቀሳውስትን ያለፍርድ አሥሮ በማሰቃየት ፤

ሠ· ከመንበረ ፓትርያርኩ ግቢ አባ ገ/ሥላሴ የተባሉትን መነኩሴ በጨለማ ወስዶ በመግደል በልደታ ቤተ ክርስቲያን ስድስት ዲያቆናትን በመረሸን እኒህንና እነዚህን የመሳሰሉትን ፈጽሞባታል ። በይበልጥ ደግሞ የሚያሳዝነው "ሥውር ምሥጢር ለማስታወቂያና መርሐ ብሔር ሚኒስቴር" በሚል ጽሑፍ በኢትዮጵያ ታላላቅ አድባራትና ገዳማት የሚገኙትን ቅርሳ ቅርሶች ደምስሶ የርእዮተ ዓለም ሙዚየም ለማድረግ አውጥቶት የነበረው ምሥጢራዊ መግለጫ ነው ። ይህንን ሁሉ ሊያደርግ የቻለው የቤተ ክርስቲያናችን የበላይ መሪ ከመሆኑ የተነሣ ነው ።

ይህንን የገለጽነው ቤተ ክርስቲያናችን አሮጌውን አስተዳደሯን አሻሽላ አዲስ አስተዳደር እንደሚያስፈልጋት ካህናትና ምእመናን እንዲዘጋጁ ለመግለጽ ያህል ነው። እንደተባለውም አሁን የሚያስፈልገው እስካሁን ድረስ ከመንግሥት ጋር የነበራትን አስተዳደር በውይይት ፈትታ እንደሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የራሷን አስተዳደር እራሷ መምራት ይኖርባታል ለማለት ነው ። እስኪ ደግሞ አንዳንድ መሰሎቻችን የሆኑትን አብያተ ክርስቲያናት እንመልከት ።

ለምሳሌ የግብፅ ኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን አሁን ከምትገኝበት የእድገትና አኩሪ ደረጃ ላይ ለመድረስ የረዳትን የመሥዋዕትነት ተግባር በአጭሩ ለመዘከር ያህል እንመልከት በአንድ ወቅት በቤተ ክርስቲያኒቱ አመራርና የመጋቢዎቿ አኗኗር ላይ በተከሠተው ድክመት የምእመናኑ ልብ መሻከሩን የተገነዘቡ እና በቤተ ክርስቲያኗ ድክመት ያዘኑ የሃይማኖት ቀናተኛ የሆኑት ምእመናን ይህን ድክመት ለማስወገድ የሚያስችል አንድ ዓይነት መንፈሳዊ እንቅስቃሴ በመፍጠር በቤተ ክርስቲያኒቱ አስተዳደር ተሐድሶ ላይ ያተኮረ አንድ ማኅበር መሠረቱ ። ይህንንም ማኅበር ወይም ጉባኤ "ትንሿ ሲኖዶስ" ሲሉ በመሰየም እንቅስቃሴያቸውን ቀጠሉ እንቅስቃሴው በካህናት በምእመናንና በወጣቶች ስለተደገፈና በቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢዎች ዘንድ ተቀባይነትን ስላገኘ የኅብረት ውይይት መድረክ ተከፈተ ። በዚህ እንቅስቃሴና ውይይት ውጤት የቤተክርስቲያኒቱ አመራር የመጋቢዎቿ አኗኗር ወደ ቀድሞ መንፈሳዊነቱ እንዲመለስ ስለተደረገ ምእመናኑ ርቀው ሳይሄዱ ለመመለስና የቤተ ክርስቲያኒቱ ቅዱስ ሲኖዶስ አባላትና በካህናቱ መካከል ያለውም መተሳሰብ የሚያስቀና ነው ። ለምሳሌ የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢዎች የወርክፍያ የሚተመነው እንደ ሐላፊነታቸው ሳይሆን እንደፍላጐታቸው ከፍተኛነት መጠን ነው ። ይህም ማለት ቤተሰብ ያላቸው ካህናት መንፈሳውያን ቢሆኑም ዓለማውያን ናቸውና ከፍ ያለ ደመዎዝ ያስፈልጋቸዋል ። አባቶችም በዓለም ቢኖሩም ገዳማውያን ናቸውና እንደፍላጐታቸው መጠነኛ ደመዎዝ ያስፈልጋቸዋል ማለት ነው ። ይህ ዓይነቱ መንፈሳዊ አኗኗርና አመራር የቤተ ክርስቲያኒቱ ምእመናን ቤተ ክርስቲያናቸውን እንዲወዱ ፡ መጋቢዎቻቸውን እንዲያከብሩና በእነሱ መንፈሳዊ አባትነትም እንዲመሩ ያደረገ ስለሆነ መልካም ምሳሌነት ያለው ነው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም አጥንታና አስጠንታ ይህን የመሰለውን አመራር መከተል ሲገባት አሁን ካለው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት የቅርብ ግንኙነት አንጻር ቤተ ክርስቲያኒቱ በአሁኑ ጊዜ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት መጋቢዎች የአኗኗርና አመራር ልምድ ማስተባበሪያ ማዕከል ወደ መሆን ደረጃ በማምራት ላይ ስለሆነች በምእመናኑና በቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢዎች መካከል አለመተማመንና መቃቃርን ሊፈጥር በሚችል ሁኔታ በመከሰት ላይ ነው ። ይህ ሁኔታ ክፉኛ ያሳሰባቸውና የወገንና የቤተ ክርስቲያን ፍቅር የያዛቸው የኢትዮጵያ መንፈሳውያን ምሁራን የቤተ ክርስቲያኒቱ አመራርና የመጋቢዎቿም አኗኗር የቀደሙ አባቶቻችንና ከዚያም የኦሬንታል ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢዎችን አመራርና መንፈሳዊ አኗኗር አርአያ የተከተለ ሲሆን ለቤተክርስቲያኒቱ አንድነትና ኅብረት እድገትና ጥንካሬ የሚበጅ እንደሚሆን ከልብ አምነው አመራሩ ይህን ሁኔታ እንዲከተል ይፈልጋሉ ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ግን እስካሁን ድረስ የግብፁን ቤተ ክርስቲያን አመራር ያልተከተለችበት ምክንያት ብዙ ድካምንና መሥዋዕትነትን የሚጠይቅ ሆኖ በማግኘቷ ሳይሆን አይቀርም ። ይሁን እንጂ የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት አመራር ድሎትና ምቾት ስላለውና ሁሉ ነገር ወደ ጳጳሳት ስለሚል ቤተሰብ ያላቸው የካህናት የችግር ኑሮ ሳይታሰብበት እንደ ኦርቶዶክሳውያን ጳጳሳቱ በምቾትና በድሎት ለመኖር ሲሉ አንዳንድ አባቶቻችን ይህ አመራር ወደ ቤተ ክርስቲያናችን እንዲገባ በመጣር ላይ ይገኛሉ ይባላል ። እንዲህ ያለው አመራር ቤተሰብ ያላቸው ቀሳውስትንና መዘምራንን ዲያቆናትንም ጭምር ጠም አሳዳሪ በመሆኑ ቤተ ክርስቲያኗ ልትቀበለው አይገባም ።

እንግዲህ ብዙ ታሪኮችን አይተናል ያለፈው አልፏል ማሰብ ወደፊት ለሚመጣው ነው ፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ የአመራር እንቅስቃሴ ለዚህ አይነት አሠራር መነሻ ምክንያት እንደሚሆን የብዙዎቻችን እምነት ነው ።

ሀ/ እስከ አሁን የነበረው ቤተ ክህነትም ሆነ ሲኖዶሱ የመንግሥት ቤተ ክህነትና ሲኖዶስ ስለነበር ወደፊት ሙሉ በሙሉ የቤተ ክርስቲያኑ የሆነ ቤተ ክህነትና ሲኖዶስ እንዲኖር ማስተማር (መስበክ)

ለ ከዚህ ዓላማ አንፃር የቤተ ክርስቲያኒቱ ሕልውና ሊጠበቅና በሁሉም ዓይነት የሥራ ዘርፍ የተሰለፈው የቤተ ክርስቲያኑቱ ሠራተኛ ወይም አገልጋይ መብት ሊከበር የሚችልበትን ደንብና መመሪያ የሚያዘጋጅ በቅዱስ ሲኖዶስ ፡ በካህናትና በምእመናን፡ በመንግሥት ወኪሎችና በሰንበት ት/ቤት ወጣቶች ውይይት ተደርጎ ስምምነት ከተደረሰ በኋላ ከሁሉም የተውጣጣ ኮሚቴ አጵቁሞ እንዲሠራ ማድረግ ፤

ሐ/ ደንቡና መመሪያው ተግባራዊ መሆኑ የሚገመገምበት የካህናት ፡ የምእመናንና የወጣቶች ዓመታዊ ጉባኤ ሊኖር የሚችልበት ሁኔታ እንዲፈጠር ማድረግ ፤

ይህ ከሆነ በሁሉም የሰው ኃይል የሚፈለገውን መንፈሳዊ አገልግሎት በምልአትና በስፋት ፡ በኅብረትና በስምምነት መፈጸም የማይቻልበት ምክንያት አይኖርም ። ከዚህ ላይ አንድ የውጭ አገር ዜጋ ያለውን መጥቀስ ለተሐ



www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ዕረፍት

## የፀባቴ አያሌው ረታ የሕይወት ታሪክ በአጭሩ፡

ፀባቴ አያሌው ረታ ከአባታቸው አቶ ረታ ንጉሤ ከእናታቸው ወ/ሮ ጥሩነሽ ዋሴ በበጌምድርና ሰሜን ጠ/ግዛት በደብረ ታቦር አውራጃ በእስቴ ወረዳ ቆማ ፋሲለደስ ከሚባለው ደብር በ፲፱፻፲ ዓ ም ተወለዱ. ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ የወላጆቻቸውን ቤት ሳይለቁ ከእናታቸው ወንድም አለቃ ላዕከ ምሕረት ዋሴ ትምህርት ጀምረው ዳዊት ደግመውቅኔና ፀዋትወ ዜማም በሚገባ ተምረዋል ። ከዚያም በኋላ በጊዜው የጋይንት አውራጃ ገዥ ወደ

ነበሩት ደጃዝማች አድማሱ ብሩ ሂደው ለጥቂት ዓመታት በጸሐፊነት አገልግለው ሲያበቁ የስማዳ ወረዳ ዋና ጸሐፊ በመሆን ለአምስት ዓመት ያህል በቅንነት ሠርተዋል ከዚያም ወደ ትግራይ ጠቅላይ ግዛት በመሄድ በዚያን ጊዜ የዓድዋና የአክሱም ገዥ ከነበሩት ደጃዝማች ተክለ ሃይማኖት ገብረ ሥላሴ ጋር ሦስት ዓመት አገልግለዋል ፡ ቀጥሎም በጊዜው የአለፋ ቋራ ጋዝጊና ሶራቆ ገዥ ከነበሩት



ፀባቴ አያሌው ረታ እኒህ ነበሩ

ፊታውራሪ ደስታ ተሰማ ጋር በመሆን በተጠቀሱት ቦታዎች እየተዘዋወሩ በፍርድ ጸሐፊነት ከአራት ዓመት በላይ ሠርተዋል ። ከዚህ በኋላ ወደ ወሎ ጠ/ግዛት በመሄድ በዚያው ወቅት የለጋአምቦ የገበራና ለገሂዳ ገዥ ከነበሩት ከደጃዝማች አመዴ አሊ ጋር በጸሐፊነት ሠርተዋል ።

በ፲፱፻፳፰ ዓ ም ጠላት ሀገራችን ኢትዮጵያን በወረራት ጊዜ ከሀገራችን ዓርበኞች ጋር በመሆን አንድ ቀን እንኳን ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ አምስት ዓመት ሙሉ በጀግንነት ተዋግተዋል ።

ከአምስት ዓመት ተጋድሎ በኋላ ሀገራችን ነፃነቷን መልሳ ስትቀዳጅ ስለተጋድሏቸው ፡

፩ኛ የአምስት ዓመት ኒሻን ፡

፪ኛ የወርቅ ሚዳይ ከቀድሞው ንጉሠ ነገሥት ተሸልመዋል ከዚያ በኋላ በኢትዮጵያ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ተመርጠው በበጌምድርና በሰሜን ጠ ግዛት ከዓባይ እስከ ተከዜ ድረስ ጸባቴ ተብለው የዕጨጌ ደብ ታዎች የሆኑትን አብያተ ክርስቲያናት አስተዳድረዋል ።

የዕጨጌ ሹም ሆነው ይሠሩበት በነበረውም ጊዜ የፈረሱ አብያተ ክርስቲያናት እንዲታደሱ ያልተሠሩት እንዲሠሩ የተሟላ ንዋየ ቅድሳት የሌላቸው እንዲሟላላቸው በማድረግ ለቤተ ክርስቲያናችን ከፍ ያለ አገልግሎት ፈጽመዋል ። ለቆማ ፋሲለደስ ለአጋጥ ጽዮን ለደንባ ጽዮን ልብሰ ተክህኖና ንዋየ ቅድሳት አበርክተዋል ። እንዲሁም በእጨጌ ስም የምትተዳደረው የድጓ ማስመረቂያ የሆነችው የቤተ ልሔም ደብር በሥሯ የሚተዳደሩ ፲፱ አብያተ ክርስቲያናት ሲኖሩ ከእነዚሁ አድባራት ከሚሰበሰበው አሥራት ሲሶው ለቤተ ክርስቲያኗ አገልጋዮች እንዲሰጥ ከመንግሥት ተፈቅዶ ሳለ ለአገልጋዮች በጠቅላላ ምንም ሳይሰጣቸው ከደብሩ የሚወለዱ

ካህናትና የካህናት ቤተ ሰቦች ብቻ እየተካፈሉ ይጠቀሙበት ነበር።

ፀባቴ አያሌው ረታ ይህ አሠራር ትክክል አለመሆኑን በመገንዘብ ለበላይ አካል አስፈቅደው ቤተ ክርስቲያኗን የሚያገለግሉ የድጓ አድራሾችና ተማሮችም እንደሞያቸው እንደ አገልግሎታቸው እንዲሰጣቸው በማድረጋቸው በድጓ አድራሾችና በሕዝብ ዘንድ ከፍ ያለ ምስጋናን አግኝተዋል ።

ፀባቴ አያሌው በዚህ ዓለም ሲኖሩ ከባለቤታቸው ከወ/ሮ የሩቅነሽ ጋር የጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም በመቀበል እጅቸው ከምጽዋት እንደበታቸው ከጸሎት አይቦዝንም ነበር ። እመቤታችን ድንግል ማርያምን ከመውደዳቸው የተነሣ ቀን በሥራ ሲደክሙ ውለው ማታ ውዳሴ ማርያም በዜማ ሳያደርሱ እራታቸውን አይበሉም ነበር ፀባቴ አያሌው በዚህ ዓለም ሲኖሩ ሁለት ወንዶች ሁለት ሴቶችበድምሩ ፬ት ልጆችን ወልደው አስተምረው አሳድገው ለቁም ነገር አብቅተዋል ። ፀባቴ አያሌው የተቸገረውን መርዳት የታመመውን መጠየቅ የተጣላን ማስታረቅ የተበደለን ማስካስ የተቀማውን ማስመለስ አዘውትረው ከሚፈጽሟቸው ሥነ ምግባራት ጥቂቶቹ ነበሩ ።

ምንም ደግ ሥራ ቢሠሩ ይህ ዓለም ለተወሰነ ዘመን መቆያ እንጂ ለዘለዓለም መኖሪያ ስላይደለ ሐዋርያው ጳውሎስ ፩ኛ ጢሞ ፬ት መልካሙን ገድል ተጋደልሁ ሩጫዬንም ጨረስኩ ሃየማኖቴንም ጠበቅሁ እንግዲህ የክብር አክሊል ተዘጋጅቶልኛል እግዚአብሔር የሚሰጠኝ በዚያች ቀን ያ ጻድቅ ፈራጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ያስረክበኛል ። ለእኔ ብቻ አይደለም መገለጡን ለሚወድ ሁሉ እንጂ ደግሞ ” እንዳለው ፀባቴ አያሌው ረታም ሃይማኖታቸውን አጽንተው ሥነ ምግባራቸውን አሣምረው እግዚአብሔርን በመፍራት ሰውን በማክበር ቤተ ክርስቲያንን በማገልገል በዚህ ዓለም እንዲኖሩ ከአምላክ የተፈቀደላቸውን መዋዕል (ዘመን) ፈጽመው ሰኔ ፲፰ ቀን ፲፱፻፸፫ ዓ.ም በተወለዱ በ፸፫ ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ቀብራቸውም የአድባራት አለቆች የገዳማት አበምኔቶች ወዳጅ ዘመዶቻቸው በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ምእመናን በተገኙበት በደብረ ታቦር መድኃኔ ዓለም ተፈጽሚል ።

እንደፀባቴ አያሌው ረታ ያለውን ታላቅ ሰው ማጣት ለቤተ ክርስቲያንም ሆነ ለቤተ ሰብእ ከባድ ጉዳት ነው ፡ ቢሆንም ኑሮ ኑሮ ሞት ዞሮ ዞሮ ቤት አይቀርም እንደሚባለው ማንም ወደማይቀርበት ሀገር ነውና የሄዱት በመልካም ሥራቸው እየተጽናናን ነፍሳቸውን በአብርሃም በይስሐቅ በያዕቆብ ቃል ኪዳን በምትወረስ በመንግሥተ ሰማያት ያሳርፍልን ዘንድ ወደ እግዚአብሔር እንጸልያለን ።

### የኃዘን እንጉርጉሮ

ከልጃቸው
ወ ሮ አስካለ አያሌው

እንዲያ ስንኮራ በአስተዋይነትህ
በትሑት ሰብእናህ በቀና ልቡናህ
ለካስ ድብቅ ኑሯል አባባ ሐሳብህ
ሕልም ነወይ ቅዠት ማመን አስቸገረን
እንደምን ጨክነ አባባ ሊለየን
ይመክረን ነበረ ዘወትር ሳይቦዝን
ከፉና በጎውን እንድናውቅ ጠንቅቀን
ጨክኖ ሞት መጥቶ በድንገት ለያየን
ድንገተኛ ጉዞህ በጣም አስጨነቀን
ምን ብለን እናልቅስ እኅዬትስ እንዘን
ልማንና ቋንቋ የለንም እንደበት
እርር አድርጎናል የአባታችን መሞት
መላ ቤተ ሰብህ ጎረቤት አዘን
መልካም ምግባርህን እያመሰዘን
በከለላነትህ ስንመካ እንዳልኖርን
በአንተው ሀብት ንብረት እንዳል ተንደላቀቅን
የአባት ወጉ ጠፍቶን ልጆችህ ተጉዳን የዜናው አቅራቢ

ቀ.ሊ.ኅ፡ ልሣን መርቅ በዛብህ ።

ድሶው ሂደት ጠቃሚ ሊሆን ይችላል ። ሰውየው ካናዳዊ ነው ፡ ስለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠለቅ ያለ እውቀት ያለው ይመስላል ። ታዲያ በኢትዮጵያ የሥራ ጉብኝት ሲያደርግ ቆይቶ ሲመለስ በሰጠው አስተያየት “እኔ እንደተረዳሁት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከካህናቱ ይልቅ የምእመናኑ ጥንካሬ የላቀ ነው በመሆኑም የካህናቱ ድክመት ለሕዝቡ ቢሆን ኖሮ ቤተ ክርስቲያኒቱ እስካሁን ድረስ በሌሎች ሃይማኖት በመዋጥ ልትኖር ባልቻለችም ነበር የሕዝቡ ጥንካሬ ለቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢዎች ቢሆን ኖሮ ደግሞ በአፍሪካ ሌሎች ሚሽኖች ገብተው ሊያስተምሩ ባልቻሉም ነበር” ሲል ትናግሯል ። ይህም የምእመናንን ብርታት የመጋቢዎቹንና የካህናቱን ድክመት ስለሚያሳይ ሁሉም በያለበት ይበርታ እንላለን ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ

# ደብዳቤ....

(ከገጽ ፫ የዞረ)

ስም ለብሰው የክርስቶስ ወገኖችን እያሉ ይመላለሱና ብኋል ማቴ ፳፬፥፫ ሐዋርያትም በተለይ ቅዱስ ጳውሎስ እኔ ከሄድኩ በኋላ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኩላዎች እንዲገቡባችሁ ደቀመዛሙርትንም ወደ ኋላቸው ይስቡ ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንደሚነሡ እኔ አውቃለሁ ስለዚህ ተጠንቀቁ ሲል ማንነታቸውን ገልጾ ተናግሯል እኛንም ከእነዚህ ተኩላዎች መናፍቃን እንድንጠነቀቅ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶናል የሐዋ.፳፥ ፳፰ ፴፩ ።

ይህ ብቻ አይደለም ስለ መናፍቃን መነሣት በብዙ ቦታ ተጠቅሶ ይገኛል ወንጌላዊው ዮሐንስም ከመናፍቃን መጠንቀቅ እንደሚያስፈልገን ሲያስገነዝብ እንዲህ

(ወደ ገጽ ፳ ዞሯል)





www.ethiopianorthodox.org

# የደብረ ሰዋስው አደሬ ቅ/ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

## በአጭሩ ፡

የአደሬ ሰዋስው ኪዳነ ምሕረት በግራኝ መሀመድ ጊዜ አደሬ ከሚባለው ስፍራ ከዋሻ ውስጥ አሁን ካለችበት ቦታ ገባች ፡ ነገር ግን የኪዳነ ምሕረት ታቦት ብቻ ሳትሆን ሌሎች ታቦታትም በዚሁ ዋሻ አሉ ይህም ሊታወቅ አባ ዓለሙ የተባሉት መነኩሴ በሚያጥኑበት ጊዜ ፲፬ ዕላቶች መኖራቸውን ለም እመናን አስረድተዋል ።

ወደ ጥንተ ታሪኩ መለስ ብለን ስንመለከት ከግራኝ መሐመድ ወዲህ አባ ተሰማ የተባሉ መነኩሴ ለዚህች ታቦት መቃኛ አሠርተው ለጥምቀት በዓል ታቦቷን አውጥተው አደሬ ወንዝ ከሚባለው ስፍራ በማ ሳደር በዓሉን አክብረዋል ፡ በዚህ ዕለት አቶ መንግሥቱ ሀብተ ማርያምና አቶ ደመርኑሬል የሚባሉ ሁለት ኢአማንያን በክርስቶስ ስም አምነው ተጠምቀዋል እኒሁ መነኩሴ ቤተ ክርስቲያን ለማሠራት አስበው በዘመኑ ከነበሩት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ለማስፈቀድ ወደ አዲስ አበባ መጡና አስፈቅደው ሲመለሱ በመንገድ እሾህ ወግቷቸው ሞተዋል ።

ከዚያም በኋላ አባ ዓለሙ የተባሉት መነኩሴ ቤተ ክርስቲያኑ እንዲሠራ በማሰብ ላይ እንዳሉ በድንገት ወደ ናዝሬት ሄደው ቀጨማ ሚካኤል ከተባለው ቤተ ክርስቲያን እንደደረሱ ታመው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ። ከዚያም በኋላ መምሬ ወልደ ትንሣኤ በድሉ የተባሉ ቄስ ከዋሻው እየገቡ ሲያጥኑ ቆይተው ወደ ጠይ ወረዳ መንጅ ባሽ ሥላሴ ለማገልገል ሄደው ሳይመለሱ በዚያው አርፈው ተቀብረዋል ።

ነገር ግን እነዚህ ሰዎች ወደዋሻው ለመግባትና ለመውጣት ሲጠቀሙበት የነበረው ከዋሻውን በስተግራ በገደሉ ላይ ተንጠልጥሎ በቅሎ የነበረው የወይራ ጫፍ ተመልሶ ወደ ዋሻው አፍ ላይ የገባ ሲሆን እነዚህ ሰዎች ከሞቱ በኋላ በጊዜ ብዛት በዋሻው ጨቲን ስለተያያዘው ተታግዷል ይጃዝማች ዘውዴ የተባሉ ሰውም ከፍተኛ ችግር ደርሶባቸው ሲጨነቁ ሳሉ አቶ ወዳጄ ጌታነህ የአደሬ ኪዳነ ምሕረት ስዕለት ትስማለችና ተሳል አሏቸው እርሳቸውም ተሳሉና ስለታቸው ስለደረሰላቸው ለታቦቷ መንበር አሠርተው ሰጥተው ነበር ።

በተጨማሪም በ፲፱፻፶፯ ዓ ም አሁን በአገልግሎት ላይ የሚገኙትን አባ ተዘራ ኃይለ ሰንበትን በወር ፴ ብር በመቅጠር የእንጨት መሰላል አሠርተው በዚያ እየወጡና እየወረዱ በማገልገል ላይ ይገኛሉ ።



ወ/ሮ ሺብሬ ተፈራ ከእማሆይ የሺ ወዳጆ ጋር

ውስጥ የኪዳነ ምሕረት ጽላት መኖሩን ሰምተው እመት አስካለ የተባሉት ሴት ከአፋፍ ላይ ሆነው በገል ዕጣን ሲያጤሱ እሳቱ እንደ ቀሰሰው ተሰውሮ ቦታውን ሳለ ጽዋው አድቶ አዲሱን ሰምቷል ።

፪. አቶ አስፋው ገብረ ሕይወት የተባሉ ምእመን የሚታጠፍ የብረት መሠላል ። አሠርተው አበርክተዋል።

፫. አቶ ባዩ ሙጃ እና አንዲት ሴት ጥዱን ሲቆርጡ ገደል ገብተው ምንም ሳይሆኑ ወጥተው እስከጊዜ ሞታቸው ድረስ የታቦቷን ተአምር እየተናገሩ ኑረው አልፈዋል ።

፬ኛ. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ቤተ ክርስቲያን እንዲሠራ አዝዘው ሳለ ተከታትሎ የሚያስፈጽም ባለመገኘቱ እስከ ፲፱፻፷፫ ዓ ም ድረስ በዚያው ዋሻ ቆይታለች በዚህ ዓ ም ዘወትር በማዕጠንት ሲያገለግሏት ለነበሩ አባ ተዘራ ኃይለ ሰንበት በራዕይ ተገልጾ ቤቴን ሥሩልኝ ፈቃዴ ነው ብላ ነገረቻቸው በዚህ ምክንያት አቶ ሽንቁጤ ተፈራ ፡ መምሬ ወንድሙ ንጋቱ የተባሉት ሰዎች በየቦታው በመዘዋወር ትንሽ ገንዘብ ሰበሰቡ ፡ በተሰበሰበውም ገንዘብ ቆርቆሮ ተገዝቶ እንጨቱም ተቆርጦና ተፈልጦ ቤተ ክርስቲያኑ በትንሹ ተሠርቶ በ፲፱፻፷፬ ዓ ም ጥር ፲፯ ቀን ታቦቷ ከዋሻው ወደ መቃኛው ቤተ ክርስቲያን ገብታለች ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ የኪዳነ ምሕረትን ጽላት አንድ ቄስ ሠርቆ ወስዶ ከጕተራ ውስጥ ከቶ ጕተራውን እንዳትከፍት ለሚስቱ ነገራት ሚስቱ ግን ምን ይሆን? ብላ ተጠራጥራ ጕተራውን ብትከፍተው የእሳት ነፀብራቅ ስለታያት ሁለት ዓይኗ ሲጠፋ ታቦቷን የሠረቀው ባሏም ታቦቷን ከጕተራው አውጥቶ በዋሻው ውስጥ አስቀምጦ አብዶ ሙቷል ።

ወ ሮ ሽብሬ ተፈራ ልጅ ስለታጣ መመባቸው የዚህችን ታቦት ተአምር በመስማት በ፲፱፻፷፬ ዓ ም ልጃቸው ታሞ በሐኪም ቤት ተኝቶ አኖራሲዎን ሊሆን ሲል ልጄን ያዳንሽልኝ እንደሆነ ጃንጥላ ገዝቼ አመጣለሁ በማለት ተስለው ሳለ ልጃቸው ኦፕራሲዮን ሳይሆን ጠጠሩ ስለወጣለትና ጤነኛ ስለሆነ የተሳሉትን ይዘው በ፲፱፻፷፭ ዓ ም የካቲት ፲፯ ቀን ከቦታው በመገኘት ስዕቷን አክብረዋል። ወ ሮ ሽብሬ ተፈራ በዚህ



ታቦቷ ከመቃኛው ወጥታ ወደ አዲሱ ቤተ ክርስቲያን ስትገባ

ብቻ ሳይወሰኑ ለታቦቷ መጐናጸፊያ ለቄሶች የሚሆን ልብስ ተክህኖ መባረኪያ መስቀል ጸናጽልና ጽንሐሕ አበርክተዋል በተጨማሪም ራሳቸውና ወ ሮ የውብዳር ተአምረ ምእመናኑን በማስተባበርና ርዳታ በመጠየቅ መንበረ ታቦት ከማሠራታቸውም ሌላ ወር ቀዘቦ ጥላ ሰጥተዋል ። ይህንንም ወ ሮ ሽብሬ ያደረጉት አባ ተዘራ ቤቴን የምታሠሩልኝ አንቺ ነሽ ብለህ ንገራት ብላ እመቤታችን ነግራኛለች ብለው ስለነገሯቸው ነው።

ወ ሮ ሽብሬ በተጨማሪ የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስን የእመቤታችን ድንግል ማርያም ሥዕልን የቅዱስ ሚካኤልን ሥዕል አሥለው ከተአምረ ማርያም ጋር በነፃ አበርክተዋል እንዲሁም አንድ ትልቅ ደወል ፡ ጠረጴዛዎችን አርባዕቱ ወንጌልንና ልዩ ልዩ መጻሕፍትን አበርክተዋል ።

ሀ. ፭፻፹ (አምስት መቶ ሰማንያ ብር)

ለ. አቶ ሀጐስን የ ብ አንድ ትልቅ የብረት መዝጊያ

ሐ. ባለቤታቸው አንድ ጠረጴዛና አንድ ተአምረ ማርያም ሰጥተዋል ።

፪ኛ ወ ሮ በላይነሽ ካሣ ከግል ገንዘባቸው ብር ፪፻፳፬.ከ፳ ሳንቲም ልጃቸውን በማሳሰብ ፫ሺ፰፻፳፰ ብር አግኝተው አበርክተዋል ።

፫ኛ አቶ ይስሐቅ ቁንቢ ብር ፱፻

፬ኛ ወ ሮ መሳይ ንጋቱ ብር ፹፻

፰ኛ አቶ ተዘራ በየነ ፯፻ ብር

፯ኛ አቶ ፈለገ ሕይወት ወ ማርያም ፰፻

፯ኛ አቶ የማነ ብርሃን ፳ ብር ከባልንጀሮቻቸው ፩፻ ብር

፰ኛ አቶ መሸሻ ፩፻፶ ብር

፱ኛ .. አስፋ አየለ ከእህታቸው የተላከ ፫፻ ብር

፲ኛ .. ጳውሎስ ባራኪ ፩ሺ፰፻ ብር

፲፩ኛ .. ዓለማየሁ ካሣ ፪፻፲

፲፪ኛ .. ካሳ ዳምጤ የእመቤታችን ሥዕል በመሥታዋት የሆነ ከእነ መጋረጃው ፲፯ የቅዳሴ ዐበል መጠጫዎች ከእነማስቀ





www.ethiopianorthodox.org

መጫቸው ፳ ብር አንድ ባኮ ሻማ አስረክበዋል ።

፲፫ኛ/ አቶ ሙሉጌታ ቀፀላ ከጓደኞቻቸው ጋር ሁለት መስኮቶች

፲፬ኛ/ እማሆይ ነበቡሽ እርዳታ ጠይቀው አንድ መስኮት

፲፭ኛ/ ወ/ሮ ጽጌ አንድ ጸናጽል ፸፩ ብር ከጧፍና ከዕጣን ጋር ሰጥተዋል ።

፲፮ኛ/ ወ/ሮ ቀለመ ወርቅ ወ/አማኑኤል አንድ የብረት መዝጊያ ትልቅ መስቀልና መጐናጸፊያ ቀፀላ ሰጥተዋል ።

፲፯ኛ/ ወጣት ሙሉጌታ ትእዛዙ ትልቅ መጋረጃ ከእነተደራቢው

፲፰ኛ/ እማሆይ የሺ ወዳጆ አንድ ቃጭልና አንድ ትልቅ መስቀል

፲፱ኛ/ ወ/ሮ በሽዋ ወ/ጻድቅ አንድ ሙዳየ ምጽዋት ከቤታቸው አስቀምጠው ፱፻፸፯ ብር ረድተዋል ።

፳ኛ/ አቶ አስፋው ገብረ ሕይወት ፪፻ ብር

፳፩ኛ/ ወ/ሮ ሙሉነሽ ጃን ሜዳ አጠገብ ንግድ ቤት ያላቸው ፍ የክዳን ቆርቆሮ ሲሰጡ ሙዳየ ሟጥን አስቀምጠው ርዳታ በማሰባሰብ ረድተዋል ።

፳፪ኛ/ እማሆይ ጽጌ ወ/ሮ ቀለሟ የላኩትን የእመቤታችን ሥዕል ያለበት የአበባ ምንጣፍ የጌታችን ሥዕልና የማርያም ሥዕል ።

፳፫ኛ/ ወ/ሮ ተዘራ አበበ ብር ፩፻

፳፬ኛ/ ወ/ሮ ቦጋለች ይምሰ ከብር የተሠራ ጽዋ ከእነማንኪያው ከክር የተሰፋ መሶበ ወርቅ፡ አዲስ ኪዳን ፡ የማርያም ሥዕል ከእነመስተዋቱ አበርክተዋል ።

ከላይ እንደጠቀስነው እቴሳተክለ ሃይማኖት ተደርባ ትኖር የነበረችው የአደሬ ኪዳነ ምህረት ታቦት የካቲት ፲፮ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ/ም ወደጥንት ቦታዋ ተመልሳ ገብታለች በገባችበትም ዕለት ካህናቱ በሽብሸባና በመዝሙር ምእመናኑ በሆታና በዘፈን በልልታና በጭብጨባ ደስታቸውን ገልጸዋል ።

ታቦቷ በዓውደ ምሕረቱ ላይ እንደቆመች ወ/ሮ የሽብሬ ተፈራባደረጉት ንግግር "እኛ ሴቶች መንፈስ ደካሞች እንደ ምንባለው ሳይሆን ሳንደክም ሳንሰለች በእናንተ ፊትና በሌሎችም ምእመናን ፊት በመቆም ለምንን ያገኘነውን ገንዘብ ከቱም ነገር ላይ እንዳዋልነው በእናንተ ዘንድ የተሠወረ አይመስለኝም ቤተ ክርስቲያኑ በአማረ ሁኔታ እንደተሠራ ሁላችንም የምንመለከተው ስለሆነ ሌላ ማስረጃ አያስፈልግም ።

ይሁን እንጂ የቤተ ክርስቲያኑ ሥራ ተጠናቀቀ ማለት አይደለም ገና ወደፊት ቀለም ኮርኒስ ሊሾ ያስፈልገዋል ። ቤተ ልሔሙም ገና ቆርቆሮ የቀረው ነው አጥር የለውም በተጨማሪም ዕቃ ቤትና የዕንግዳ ማረፊያ ደጀ ሰላም እንዲሁም መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ለመሥራት ዕቅድ ስላለን ይህንኑ ዕቅዳችን ለማስፈጸም የምንችለው ከእናንተ ከእመቤታችን ወዳጆች እርዳታ በመጠየቅ ነው በአሠሪነት ከእኔ ጋር የሚደክሙ ወ/ሮ ላቀች ስሚና እማሆይ የሽ ወዳጆ ናቸው ። ካሉ በኋላ ለህገራችን ሰላምን ፍቅር አንድነትን ተመኝተው የዕርዳታ እጃቸውን ለሚዘረጉ ምእመናን የስልክ ቁጥራችን ፺፩ ፳፬-፩፬ ነው ዕቅዳችን ሁሉ ከፍጻሜ ለማድረስ እንድንችል ኃያሉ እግዚአብሔር በቸርነቱ ይርዳን በማለት ወ/ሮ የሽብሬ ተፈራ ንግግራቸውን አጠቃለዋል። ከዚያም በኋላ በአቡነ ኤፍሬም ምዕራገ ጸሎት ተደርጐ ታቦቷ ወደመንበረ ክብሯ ገብታለች ።

በአብቹና ጠራ አውራጃ
የደብረ ሰዋሰው
አደሬ ቅድስት ኪዳነ
ምሕረት ቤተ ክርስቲያን
ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት

# ልማት በደብረ ከዋክብት

ከአዲስ አበባ በስተ ደቡብ ከሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት አንዱ የደብረ ከዋክብት አቡነ አረጋዊና ቅዱስ ገ/ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ነው ። የደብረ ከዋክብት አቡነ አረጋዊና ቅዱስ ገ/ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ልዩ የሚያደርገው ነገር አለ ይህም በቤተ ክርስቲያኑ አጠገብ የሚገኘው አለርት የተሰኘው የመላ አፍሪካ የሥጋ ደዌ መከላከያ ሆስፒታል ይገኝበታል ። ሆስፒታሉ ከቤተ ክርስቲያኑ ጋር በአለው መቀራረብና ግንኙነት እንዲሁም ቤተ ክርስቲያኑ በድሆች ከተማ የተመሠረተ በመሆኑ ሆስፒታሉ ቤተ ክርስቲያኑን በአንዳንድ ነገሮች የሚረዳ ሲሆን የደብሩ አገልጋዮች ካህናትን በህክምናም ሆነ በሌላው ማኅበራዊ ችግር ይረዳል።

ሌላው ደግሞ ቤተ ክርስቲያኑ የተመሠረተው በ፲፱፻፵፪ ዓ/ም ሲሆን ሰፊ የሆነ ቦታ ያለውና በደብሩ ዙሪያ ተንጣሎ የሚታየው ሜዳ አብዛኛው የቤተ ክርስቲያኑ ክልል ስለሆነ አያሌ የልማት አውታሮችን ለመዘርጋት የሚያስችል ነው ። በዚህም መሠረት በቤተ ክርስቲያኑ አስተዳደር ብዙ የልማት ሥራዎች ተከናውነዋል ።

በደብሩ የተከናወኑትን የልማት እንቅስቃሴዎች ለመመልከት ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ጽ/ቤት የተላከ አንድ ጋዜጣኛ በሥፍራው ተገኝቶ ነበር ።

በቦታው ለተገኘው መልዕክተኛ እንደተገለጠው የደብሩ አስተዳዳሪ መልአከ ብርሃናት አደራው ንጉሤ የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ አያሌ የልማት ሥራዎች ተከናውነዋል ። ከነዚህም መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው ።

፩ኛ/ እጅግ በጣም ሰፊ የሆነ የስብከተ ወንጌል አዳራሽ ከነእስቴጁ በአማረ ሁኔታ ተሠርቶ ወንጌላዊ አገልግሎት እየተሰጠበት ይገኛል ።

፪ኛ የክርስትና ቤት ከነማጥመቂያው ዘመናዊ በሆነ አሠራር ተሠርቶ ተገቢው መንፈሳዊ አገልግሎት እየተፈጸመበት ይገኛል።

፫ኛ/ ድሮ ዳቦ ቤት የነበረው በመፈራረሱ በዘመናዊ ሕንፃ አሠራር ሦስት ክፍሎችን የያዘ ሕንፃ ከነሻይ ክበቡ እጅግ በአማረ ሁኔታ ተሠርቶ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

፬ኛ/ የደብሩ አስተዳዳሪ መልአከ ብርሃናት አደራው ንጉሤ በአካባቢው ሕዝብ ያለውን የእህል ወፍጮ ችግር በመመልከት ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ጽ/ቤት ጉዳዩን በማቅረብ የእህል ወፍጮ በእርዳታ እንዲሰጥ በመፈቀዱ የእህል ወፍጮ ቤት ከነመጋዘኑ በአማረ ሁኔታ ተሠርቶ በእርዳታ የተገኘው የእህል ወፍጮ በመተከል ላይ ይገኛል ።

፭ኛ/ የደብሩ አስተዳዳሪ መልአከ ብርሃናት አደራው ንጉሤ ከአካባቢው ምእመናን ጋር በአላቸው መግባባት የአካባቢውን ሕዝብና እድሮች አስተባብረው በቤተ ክርስቲያኑ ዙሪያ ዘመናዊ የሆነ መጠለያ ተሠርቶ ምዕመናኑ ለማስቀደስና ለጸሎት ይጠቀሙበታል ።

፮ኛ/ በቢሮ አካባቢ ያለው የሥራ እንቅስቃሴ ሲሆን የደብሩ አስተዳዳሪ መልአከ ብርሃናት አደራው ንጉሤ ሥራ ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ አሠራሩ ከነበረው ተሻሽሎ ጥራትና ብቃት እንዲኖረው ለማድረግ የተለያዩ የቢሮ ጠረጴዛዎችና ወንበሮች እንዲሟሉ ተደርጓል ። እንዲሁም በእንግሊዘኛና በአማርኛ የወረቀት ማዘጋጃዎችን በማሟላትም ዘመናዊ ታይፕ ራይተር በመግዛት ከነበረው አሠራር ተሻሽሎ በቅልጥፍና እና በጥራት የሚሠራ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል ።

፯ኛ/ በደብሩ አካባቢ ዘመናዊ የመጸዳጃ ቤት ፬ ክፍሎች የአሉት ሲሆን ተሠርቶ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል ። እንዲሁም ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በተደረገው የሥራ ግንኙነት ከሚኒስትሩ መ/ቤት የተገኙት አያሌ የጽድና የባህር ዛፍ ችግኞች በአማረ ሁኔታ ለምልመው በመታየታቸው ለቤተ ክርስቲያኑ የሰጡት ውበት ከማስደሰቱም ሌላ በአሁኑ ዓመት ደግሞ ከ፫ሺ በላይ የሆኑ የተለያዩ ችግኞች ተተክለው በመጽደቅ ላይ ይገኛሉ ።

፰ኛ/ የቤተ ክርስቲያኑ ቤተ መቅደስና ዕቃ ቤቱ በመታደስ ልዩ ውበት ሰጥቶት ይገኛል እንግዲህ ከብዙ በጥቂቱ የልማቱ ይዘት ይህንን ይመስላል ።

## መንፈሳዊ አገልግሎትን በተመለከተ

በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ለሚሰጠው መንፈሳዊ አገልግሎት የተመደቡ በቂ የሆኑ ካህናት ዲያቆናትና መዘምራን ሲኖሩ የአብነት መምህራንም ተሟልተው ይገኛሉ ።

## ስብከተ ወንጌልን በተመለከተ

በደብረ ከዋክብት አቡነ አረጋዊና ቅዱስ ገብረ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በደብሩ አስተዳደር የሚመራው የስብከተ ወንጌል ኮሚቴ የአለው ሲሆን ለምዕመናን የሚሰጠው ስብከተ ወንጌል ጥራትና ብቃት በአላቸው የደብሩ መምህራንና መዘምራን በጥራት ይካሄዳል ።

የሰንበት ት ቤትን በተመለከተ የደብረ ከዋክብት አቡነ አረጋዊና ቅዱስ ገ/ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ት ቤት ከሌሎች የአዲስ አበባ አድባራት ልዩ የሚሆንበት ነገር አለ ይህም በዚህ ሰንበት ት/ቤት ተማሪዎችን በመደበኛ መምህርነት የሚያስተምሩ የደብሩ የመጽሐፍና የቅኔ አብነት መምህር የሆኑት

መሪ ጌታ ፈንቴ አበበ ስለሆኑ ወጣቶች የሚአገኙት መንፈሳዊ እውቀት ከፍተኛ መሠረት ያለው



www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ሞት

## ግራ ጌታ አቦዬ በ፩፻፫ ዓመታቸው አረፉ

ግራጌታ አቦዬ በ፲፰፻፸፰ ዓ/ም ከእናታቸው ከወ/ሮ ፈንታዬ ወን ድማገኘሁና ከአባታቸው ከአቶ ይሄይስ ገብሬ በሸዋ ክፍለ ሀገር በሎሚ ወረዳ ተመለዱ ። ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ በትውልድ አገራቸው ልዩ ስሙ ኩማዬ አማኑኤል ከተባለው ደብር ንባብ ተምረዋል ። ከዚያም ወደዝቋላ ሔደው ከአለታ ገብረ ኢየሱስ ዘንድ ቅኔ ተቀኝተዋል ። ቀጥሎም ፀዋትወ/ዜማ ከተማሩ በኋላ ወደደብረ ሊባኖስ ሄደው የቅኔ ትምህርታቸውን እያስፋፉ በተጨማሪም የመጻሕፍት ትርጓሜን ተከታትለዋል።



በዓለማችን ላይ ፻፫ ዓመት የኖሩት ግራ ጌታ አቦዬ

በደብረ ሊባኖስ ገዳም ለትምህርት በቆዩበት ዘመን ለራሱ ብቻ ዕውቀት ልገብይ ሳይሉ በገዳሙ ከሚኖሩት መነኮሳት መካከል ለብዙዎቹ ማታ ማታ የቃልትምህርት በማስቀጸል መንፈሳዊ አገልግሎት አበርክተዋል ። በዚሁ ገዳም ለመንፈሳዊ አገልግሎት ከሁሉም ቀድመው የሚገኙ በመሆናቸው ከገዳሙ ኃላፊዎችና ኅብረተሰብ የተለያየ አክብሮትንና አድናቆትን አገኝተዋል ።

በ፲፱፻፲ ዓ/ም ወደ አዲስ አበባ መጥተው በዚህ በታላቁና በጥንታዊው በቀራንዮ መድኃኔዓለም ደብር ከታወቁት መምህር ከሊቀ ጠበብት ወልደሐና ዘንድ ዜማ ተምረዋል ። እንዲሁም ወደ አዲስ አበባ ቅድስት ሥላሴ ሄደው ከቀኝ ጌታ ወልደ ጊዮርጊስ ዘንድ ይህንኑ የዜማ ትምህርታቸውን በበለጠ አስፋፍተዋል ። እንደገናም ወደዚሁ ወደ ቀራንዮ መድኃኔ ዓለም ደብር ተመልሰው ማለትም ከጠላት ወረራ በፊት በ፲፱፻፲፩ ዓ/ም ንባብና ዜማ ማስተማር ጀመሩ ። የወቅቱን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት በትጋትና በተሟላ ሁኔታ ማስተማራቸው በበላይ አካል ዘንድ ስለታወቀ ሽልማት እንዲሰጣቸው ተወስኖ በዚያን ወቅት የደብሩ አስተዳዳሪ በነበሩት አማካይነት ከመንግሥት የተላከላቸውን ሽልማት ከምስጋና ጋር ተቀብለዋል ። በዚሁ በመምህርነት ሞያቸው ባሳዩት ትጋትና ችሎታ በተደጋጋሚ እየተሸለሙ የሙያቸውንብቃት አስመስክረዋል ።

በቅኔ ሞያቸውም የተደነቁ በመሆናቸው ለሽልማት ካበቃቸው አንዱ ይኸው ነው የቅኔን ምሥጢር ወደ ውስጥ ዘልቆ የማመንጨት ሞያ ስላላቸውና ብልህ አስተዋይ ስለነበሩ ሲራክ የሚል የቅጽል ስም ተሰጥቷቸው ሲጠሩበት ኖረዋል ። በ፲፱፻፳፯ ዓ/ም ከብፁዕ አቡነ አብርሃም ዘንድ ቀርበው የቅስና ማዕረግ ተቀብለው የሥልጣነ ክህነት ባለቤት ለመሆን በቅተዋል ። ጠላት ድል ሆኖ ከአገራችን ከተባረረና ነፃነት እንደተመለሰም የማስተማር ሥራቸውን አስፋፍተውና በርካታ ወጣቶችን በበለጠ አሰባስበው ትምህርቱን በትጋት እንዲገበዩ አድርገዋል ። በዚሁ ሞያቸው ከቤተ ክህነት የመምህርነት ደመወዝ በየወሩ እየተከፈላቸው ስማቸው በመምህራን የሞያ መዝገብ ውስጥ እንዲሰፍር ተደርጓል ።

የዕድሜ ፀጋን የተላበሱት እኚህ ታላቅ አባት ያለ መታከት ለዘመናት በአደረጉት ሰውንበዕውቀት የማነፅ ጥረታቸው በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ተማሪዎች የአገራቸውን ትምህርት በሚገባ አውቀው ለዘመናዊው ትምህርት የተሟሉ ሆነው እንዲገኙ አብቅተዋቸዋል። ዛሬ በግል ሥራ የሚተዳደሩትን ጨምሮ በተለያዩ መሥሪያ ቤቶችናድርጅቶች ተሠማርተው የሚገኙ የቀድሞ የግራጌታ አቦዬ ተማሪዎች ቁጥር እጅግ ከፍተኛ ነው ቢባል ከእውነት መራቅ አይሆንም ። ከነዚህም መካከል በወታደራዊ መስክ እስከ ጄኔራል ፣ በሲቪል ሥራ ደግሞ እስከ ዶክተርነት የደረሱ ይገኙባቸዋል ።

ግራ ጌታ አቦዬ ተማሪዎቻቸው ትምህርት በትጋት እንዲከታተሉ በሚያደርጉት ጥረት በማስተማርና በጸሎት ለደከመ ሰውነታቸው እንኳ ፋታ ባለ መስጠት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ከመደበኛው የማስተማሪያ ጊዜያቸው ውጪ በቤታቸው ውስጥ ሆነው በማስተማር ዕውቀታቸውን ያካፈሉ ደግ የቀለም አባት ነበሩ ። ከዚህም ጥረታቸውና ጽኑ እምነታቸው የተነሳ ተማሪዎቻቸው ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደ ዘመናዊ ትምህርት ለመሸጋገር ጊዜ አይወስድባቸውም ነበር ።

ግራጌታ አቦዬ በአንድ በኩል ዜማ በሌላ በኩል ንባብ እያስተማሩ የትምህርቱ ሂደት አድማሱን እንዲያስፋና የቀለም ምርት በጥራት እንዲመረት በማድረጋቸው የዚህ ደብር አካባቢ ወጣቶች ብቻ ሳይሆኑ ከሌሎችም አካባቢዎች ወደ ግራጌታ አቦዬ ዘንድ ለትምህርት የሚጐርፍ ተማሪ ብዛት ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ እንዲሄድ አድርጐት ነበር ።

ግራ ጌታ አቦዬ በቀለም አባትነታቸው ብቻ ሳይወሰኑ ተማሪዎቻቸው ለአገርና ለወገን መልካም ሥራ ሠርተው መልካም ዜጋ እንዲሆኑ እንደወላጅ አባት አዘውትረው ምክር የሚለግሱ በመሆናቸው በተማሪዎቻቸው ዘንድ ልዩ አክብሮትና ትኩረት እንዲሰጣቸው አድርጓቸዋል ። እኚህ ታላቅ አባት የዕድሜያቸውን እኩሌታ በማስተማር ሥራ ላይ ያዋሉ ከመሆናቸውም ሌላ አንደበታቸውን በጸሎት ያስገዙ ፣ ትሁትና መንፈሰ ጠንካራ አባት ነበሩ ። በተለይም ሰውን ማክበር ቀና ምክር መለገስ ዕውቀትን ማካፈል ፣ ትዕግሥትና ትህትና ፣ ቅንነትና ርህሩህነት ለግራጌታ አቦዬ የተሰጡ የግል ሀብቶቻቸው ነበሩ ቢባል ማጋነን አይሆንም ።

በዘመናቸው ሁሉ በአንደበታቸው ክፉ ነገር ተናግረው የማያውቁ ሰውን በእኩልነት የሚመለከቱና ከጸሎትና ለሰው አክብሮትን ከመለገስ በቀር ከአንድ ሰው ጋር እንኳ በፀብና በቂም ያልተገናኙ እግዚአብሔር ያዘዘውን በጐ ሥራ ሁሉ የፈጸሙ እውነተኛ የቤተ ክርስቲያን አባት መሆናቸውን በተግባር ያስመሰከሩ እጅግ በጣም ደጋግ የሆኑ አባቶች ያገኙትን የዕድሜን ፀጋ የታደሉ ነበሩ።

ግራ ጌታ አቦዬ ለትምህርት በተዘዋወሩባቸው ገዳማትና አድባራት ሁሉ በበጐ ተግባራቸውና በቅን አመለካከታቸው በምግሌነት ሲታዩ የኖሩ እድለኛ አባት ነበሩ ። በዚህም በቀራንዮ መድኃኔዓለም ደብር ባሳለፏቸው አያሌ ዘመናት ስለመልካም ተግባራቸውና ተወዳጅነታቸው ስለትሕትናቸው ለስብዕናቸውና አርአያነታቸው ከፍተኛ አክብሮትና አድናቆት የተቸራቸው አባት መሆናቸውን የማይመሰክር አይገኝም ። ግራ ጌታ አቦዬ ከሁሉም በላይ ትጉህ የቀለም ገበሬ ነበሩ ። በተማሪዎቻቸው አእምሮ የዘሩት የቀለም ዘር በወንጌሉ እንደተጻፈው በሾህ መካከልና በጭንጫ ላይ እንደተዘራው ዘር ሆኖ አልቀረም። በጥሩ መሬት እንደተዘራው መልካም ዘር በእጥፍ ለምቶ ለፍሬ በቅቷል ። ዛሬ በሥራ ዓለም የሚገኙ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ የእርሳቸው ደቀ መዛሙሮች ሁሉ የመልካሙ እርሻ ውጤት ማስረጃዎች ናቸው ። በሌላ አነጋገር እነዚህ በቀለም የተወለዱ ደቀመዛሙርቶቻቸው የግራጌታ አቦዬ የረጅም ጊዜ የድካም ፍሬዎች ናቸው ማለት ነው ።

ከቀለም አባትነታቸው ሌላ ከእግዚአብሔር በታደሉት መንፈሳዊ ባህሪያቸው በሁሉም ዘንድ በአንክሮ የሚታዩና ወጣቶችን አስተምሮ ለቁም ነገር በማብቃት ልዩ ስጦታ ያላቸው እኚህ አባት አንድ ታሪክ የተፈጸመበትን ጊዜና ዘመን በሀሊናቸው መዝግቦ የመያዝ ችሎታ ስላላቸው በአንድ ወቅት ለተፈጸሙ ድርጊቶች ሁሉ ምስክርም ማስረጃም ነበሩ ። ፍቅርና መግባባት በሰዎች መካከል እንዲኖር አጥብቀው የሚመኙ አባት ሲሆኑ ታዛዥነትን የሚወዱ ሕገ እግዚአብሔር ...

ነው ። በዚህ ሰንበት ት ቤት የሚማሩት ወጣቶች ብቻ ሳይሆኑ ዲያቆናትና ሌሎችም ከፍተኛ የመንግሥት ሥራ ያላቸው ወጣቶች ጭምር ናቸው የትምህርቱም አሰጣጥ በእጅጉ የሚያስደስት ሲሆን የሚሰጡትም የትምህርት አይነቶች የሚከተሉት ናቸው ።

፩ኛ መሠረተ እምነት

፪ኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

፫ኛ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንና ሌሎችም ይገኛሉ ።

በዚህም የትምህርት አሰጣጥ መሠረት ለወጣቶችና ለትንንሽ ሕፃናት በፕሮግራም ይሰጣል በዚህም ፕሮግራም መሠረት ለሕፃናት ዘወትር ቅዳሜ ከ፱ ፣ ፲ በአለው ጊዜና እሁድ ዘወትር ከ፰ ፲ ባለው ጊዜ ለሕፃናቱ ተገቢ የሆነ ትምህርት ሲሰጥ ከፍ ላሉ ወጣቶች ደግሞ ቅዳሜ ከ፰ ፲ ባለው ጊዜና እሁድ ከ፱ ፲ ባለው ጊዜ ወጣቶችን የሚስብ መንፈሳዊ ትምህርት ይሰጣል ።

በተለይ በዚህ ሰንበት ት ቤት የሚሰጠው ትምህርት በበቂ ሁኔታ በመሰጠቱ የአያሌ ወጣቶችን ዕድል በጥሩ ሁኔታ ለወደፊቱ አመቻችቷል ። እንግዲህ ከብዙ በጥቂቱ የደብረ ከዋክብት አቡነ አረጋዊና ቅዱስ ገብረ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የልማት እንቅስቃሴና መንፈሳዊ አገልግሎት በዚህ አይነት እንደሚከናወን ተረድተናል ።

የዜናው አቀራቢ

መሪጌታ ኤፍሬም በየነ





www.ethiopianorthodox.org

ቀው በጾም በጸሎት የኖሩ እውነተኛና ቅን አባትም መሆናቸውን በድጋሚ እንመሰክራለን ።

ግራጌታ አቦዬ በዚህ ታላቅ ደብር ከቃል ትምህርት ሌላ ንባብና ዜማ ከሃምሣ አመት በላይ አስተምረዋል ። በእነዚህ ዓመታት በቤተ ክርስቲያን የሰጡትን መንፈሳዊ አገልግሎት ይጨምራል ። በአጠቃላይ ሲሰላ ግን በዚህ ደብር ከ፷፭ ዓመታት በላይ አገልግለዋል ። በዚህም ጊዜ ውስጥ የመሪጌታነትና የግራ ጌታነት ማዕረግ አግኝተዋል ።

ጡረታም ከወጡ በኋላ ደከመኝ ልረፍ ሳይሉና የዕድሜ ገደብ ሳይገዳቸው በአላቸው የቤተ ክርስቲያን ፍቅር የተለመደ መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን ከማበርከት የተቆጠቡበት ጊዜ አልነበረም ። በ፲፱፻፺፩ ዓ ም ከወ ሮ ከበቡሽ ወ አረጋይ ጋር ጋብቻ ፈጽመው ፯ ልጆችን በማፍራት ቅድመአያት ለመሆን በቅተዋል ። ዳሩ ግን ሞት የማይቀር እዳ በመሆኑ ሐምሌ ፫ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ ም በተወለዱ ፶፫ ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ። የቤተ ክርስቲያናችን አባት የነበሩት እኒህ ታላቅ ሰው በሞት በመለየታቸው ይህ ደብር አንድ ታዋቂ ምስክር አጥቷል ። ቀራንዮ የመጨረሻውን የሰው ምስክሯንና ማስረጃዋን ያጣችበት በመሆኑ ኀዘኗ መሪር ነው ። ሆኖም በሞት ቢለዩንም ዕውቀታቸውን አካፍለው ለሀገርና ለወገን ባበረከቱት ድርሻ ስማቸው ሕያው ሆኖ ይኖራል ። ስለዚህ ለባለቤታቸውና ለልጆቻቸው መጽናናትን እንዲሰጥልን እየተመኘን ለመጨረሻ ጊዜ እንሰናበታቸዋለን ። ግራጌታ አቦዬ ብዙ ሕዝብ እንዲሁም ዘመድና

# ደብዳቤ...

ከገጽ ፲፫ የዞረ)

ይላል የሥራችሁትን ይመወዝ እንዳታጠፉ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ ሲል ያስጠነቅቃል የዮሐ· ፪ኛ መልእክት ቁጥር ፱ ። እነዚህ መናፍቃን ከየት መጡ ከየትስ ተነሡ ስለምትለውም መናፍቃኑ ከዚች ከኦርቶዶክስ ተነጥለው የሄዱ አሉ እንደዚሁም ከዚህ ከተነጠሉ በኋላ እርስ በእርሳቸው እየተነጠሉ እነሆ በሺ የሚቆጠሩ ይገኛሉ ።

ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ሃይማኖት ግን አምላካችን ክርስቶስ ከመሠረታት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በዚሁ ጸንታ ትገኛለች የተጠቀሱትን ጥቅሶች በሚገባ መላልሰህ ተመልከታቸው ።

፱ የወንዶችና የሴቶች አቋቋም የተለያየ ነው በአዲስ አበባ ግን አንተ እንደምትለው ሴቱም ወንዱም አብረው ቁመው ይታያሉ እውነትህ ነው ይሁን እንጂ ይህም ቢሆን በሥነ ሥርዓት በሚገባ የሚቆሙም በአዲስ አበባ ሁሉ አይደለም ነገር ግን እንደዚህ ሊሆን የቻለው ከአመራሩ ጉድለት ነው እንጂ አንዳንድ የደብር አለቆች እናንተ በዚህ ቁሙ እናንተም በዚህ ግቡ ብለው ቤተ ክርስቲያናቸውን አስከብረው እንደሚገኙ ሁሉ የሴቶቹንና የወንዶችን መግቢያ ለይተው ያላወቁ ያሉበት ቤተ ክርስቲያንም ያሉት አስተዳደሪዎች እንደሚያስተካክሉት ተስፋ እናደርጋለን ።

፲/ በቅዳሴ መካከል ለምን ትምህርት ይሰጣል ስለምትለው የተነበበውን ማብራራት ተገቢ ነው እሱም እንደ ቅዳሴ ይቆጠራል እንጂ ከቅዳሴ ተነጥሎ የሚታይ አይደለም ። ፲፩/ ከዚህ በላይ የጠቀስካቸው ሁሉ እውነት የሌላቸው ናቸው በቅዝቃት ባሕር ተውጠው ያልሆነውን ወሬ ሲያናፍሱ ይሰማሉ እንጂ እውነተኛነት የላቸውም ውሸታቸውም ከዕለት ወደ ዕለት እየተገለጠ ነው ለምሳሌ ዓለም በዚህ ቀን ታልፋለች ብለው ከዚህ በፊትም የተናገሩ ነበሩ ነገር ግን እነሱ ባሉት ቀን አላለፈችም እመቤታችን ታየችን እመቤታችን ተናገረችን የሚሉም ሁሉ ውሸተኞች የሐሳዊ መሲህ መንገድ ጠራጊዎች ናቸው እንጂ እውነተኞች አይመስሉም ።

እርግጥ እመቤታችን አትታይም አንልም ነገር ግን እመቤታችን ማየት የሚቻለው ወይም ልትገለጽ የምትችለው በጾም በጸሎት ተወስነው ሕገ እግዚአብሔርን አክብረው በሥጋው ወደሙ ተወስነው የለመንዋትና የተማፀንዋት በትክክል ያዩአታል እርስዋም ትገለጽላቸዋለች ከዚህ በተረፈ በኃጢአት ተበክሎ ከመንፈሳዊ መንገድ ርቆ በጾም በጸሎት ጽሙድ ሆኖ ያላገለገለና በሥጋው በደሙ ያልተወሰነ ሰው ከእመቤታችን ጋር ተነጋገርኩ እመቤታችንን አየሁ የሚል ሰው የቅዠት ራእይ እንጂ እውነተኛ ራእይ ያየ ያለ መሆኑን መገንዘብ ይኖርብሃል ለዚሁም የምሰጥህ ማስረጃ የቅዱስ ጳውሎስ ቃል ነው አጋንንትና መናፍቃን በተለያየ መንገድ መምጣታቸውን በማስመልከት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ

---

ወዳጅ በተገኘበት በቀራንዮ መድኃኔ ዓለም ሐምሌ ፬ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ/ም የቀብራቸው ሥነ ሥርዓት ተፈጽሟል ።

ከቤተሰቦቻቸው

# የሴቶች ዓምድ

## የ ዋ ይ ታ ድ ም ፅ

አዘጋጅ መዓዛ አስማማው

ይህ ድምፅ በመራራ እንባ ታጅቦ የተሰማው መቼ ነበር ? እንዴት ዓይነት ዋይታ እንዴት ዓይነት መራራ ልቅሶ ቢለቀስ ነው ከምድር ወደ ሰማይ የደረሰው? አልቃሹስ ምን ያህል መከራ ቢደርስበት ምን ያህል ግፍ ቢፈጸምበት ይሆን የመረረ ልቅሶ ድምፅ ሊያቀርብ የተገደደው ? በእግዚአብሔርስ ዘንድ ምን ያህል እምነትና ምግባር ቢኖረው ነው ? ለመሆኑ እንባውን የረጨው ከጸሎትና ከምህላ ጋር ወይስ ልቡን ለእግዚአብሔር በመስጠት?

እነዚህን ጥያቄዎች የምንመልስ ሰው በቀጥታ ታሪኩ ከሚገኝበት ከታላቁ መጽሐፍ ቅዱሳችን ይሆናል በትንቢተ ኤርምያስ ም ፴፩ ቁ ፲፭ ላይ የዋይታና የመረረ ልቅሶ ድምፅ በራማ ታሰማ ፡ ራሄል ስለልጆችዋ አለቀሰች ፡ የሉምና ፣ ስለ ልጆችዋ መጽናናትን እንቢ አለች" ይላል ። ነቢዩ ኤርምያስ እንባውና ጸሎቱ ከሰማይ የደረሰለትን ሰው በግልጽ አሳውቆናል ። ከሴቶች መካከል ራሄል መሆኗን በዚሁ ቁጥር ላይ ይገልጻል ። ይሁን እንጂ የተፈጸመባትን ግፍና የደረሰባትን መከራ አብራርቶ አላሳየንም ቢሆንም የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት በአንድምታ ሰፋ ባለ መልኩ አትተውታል ።

ሐተታው እንደሚለው እሥራኤላውያን በግብጽ ባርነት በሚገዙበትና የፈርዖንን ፒራሚድ በሚሠሩበት ወቅት ሴቶች ሳይቀሩ ጭቃ ሲረግጡ ድንጋይ ሲያግዙ ይውሉ ነበር ። ወንድ ወንዶቹንም ከእናቶቻቸው ለይተው ወደ ወንዝ ሲጥሏቸው የእናት ሆድ አይችልምና ያዝኑ ይተክዙ ነበር ። በተለይም ራሄል የምትወልድበት ወር ደርሶ ጭቃ ሲያስረግጧት ሳለ ደከሟት ቆም አለች ። አሠሪውም መቆሚን ስላየ ለምን አትሠሪም ? ብሎ በያዘው ዱላ ሆዷን መታት። በዚህ ጊዜ ጽንሱ ከምትረግጠው ጭቃ ላይ ወደቀ ለማንሳትም ብትሞክር የሠራተኞቹ ግብጻዊው አለቃ የሰውሥጋና ደም ጭቃውን ያጸናዋል እንጂ ምን ይለዋል? አብረሽ እርገጭ ! ሲል አዘዛት ።

ራሄልም እግዚአብሔር የሰጣት ጸጋዎች ልጆች አልሆኗትም ሞተዋልና ልቅሶ መተውን አልወደደችም ። እንዲያውም "ኢ.ሀሎኑ በዝ ሰማይ አምላክ እሥራኤል" እግዚአብሔር የለምን? እያለች እንባዋን በእጇ ተቀብላ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን መንበረ ጸባዖት ረጨችው" የዋይታ ድምጿም በሰማይ ተሰማ እግዚአብሔርም የደረሰውን የግፍ ግፍ ተመልክቶ ያኮረበችውን እንባ አይቶ ጸሎቷን ተቀብሎላታል "ድምፅሽን ከልቅሶ ዓይንሽንም ከእንባ ከልክይ ለሥራሽ ዋጋ ይሆናል ። የሚል ምላሽ በቁ 16 ላይ እናገኛለን በእውነቱ እሥራኤል ከግብጽ ባርነት ሊላቀቁ የቻሉት በስይፋቸውና በጦራቸው ወይም በፈረጠመ ክንዳቸው ማይሆን በቀረበው መራራ እንባ መሆኑን ተረድተናል ።

እንግዲህ ወደሀገራችን ወደ ኢትዮጵያ መለስ ያልን እንደሆነ ኢትዮጵያ የራሄል ምሳሌ ሆና እናገኛታለን ። ልጆቿ በርስ በርስ ቅራኔዎችና ውስብስብ በሆኑ ነገሮች ሆድና ጀርባ ሆነው ባሳለፏቸው ዘመናት እጅግ ስታዝን ኖራለች። በሥልጣን ላይ የነበሩት አረመኔዎች በሀገሪቱ ተወላጆች ወገኖቻቸው ላይ የደም ጥማታቸውን ለማርካትና የሞት ጽዋ ለመጋት መሽቀዳደምን የጀመሩት ገና ከመነሻቸው ነበር ። የቃለ መሐላቸውን ቃል ኪዳን የወንድሞቻቸውና የእህቶቻቸው ደም እንደነበር አይዘነጋም። የግድያ አፈጻጸማቸው ሂደትም "ማነህ ባለማም

---

ተማሪ ፍሥሐ ሲሳይ ያቀረብካቸው ጥያቄዎች በጣም ተፈላጊዎች ናቸው በመልሳቸውም እንደምትረካ ተስፋ እናደርጋለን ።

መ ክንፈ ርግብ ማርቆስ

ይላል እንደ "እነዚህ ያሉ ሰዎች የክርስቶስን ሐዋርያት እንዲመስሉ ራሳቸውን እየለወጡ ውሸተኞች ሐዋርያትና ተንኮለኞች ሠራተኞች ናቸው ይህም የሚያስደንቅ አይደለም ሰይጣን ራሱ የብርሃን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና" ፪ኛ ቆሮ· ፲፩ ፡ ፲፫ ስለዚህ እነዚህን አትመኗቸው አትከተሏቸውም ፡ ይላል ።

፲፪ የማቴዎስ ወንጌል ፳፬ ፡ የጠቀስከው በ፳ኛ ተራ ቁጥር ያብራራሁት ስለሆነ ተጨማሪ የሚያስፈልገው አይመስለኝም ።



www.ethiopianorthodox.org

"ንት" እያሉ ያመርቱና ይመረረቱ እንደነበር ይታወሳል ። ትዝታንቱ ግን የሚታወስን ፍፁም በግፍ በሆነ መልኩ ነው።

ዲያቆናት ቀሳውስት ተማሪዎች ሠራተኞች ሳይባሉ የማኅፀኗ ፍሬ የሆኑ ልጆቿ በግፍ ሲገደሉባት ፣ በእሥራት ሲማቅቁ ፣ በግርፊያ በስደት ሲንገላቱ በጠቅላላው ያለእውነተኛ ፍርድ በምድራዊ የሐሰተኛ ፈራጆች እጅ ተይዘው ቁምስቅላቸውን አይተዋል ። በተለይም የዛሬ አበባዎች የነገ ፍሬዎች ቤተ ክርስቲያኒቱንና ሀገሪቱን ይረከባሉ ተብሎ ተስፋ የተጣለባቸው ዜጎቿ (ብዙ ሺህ ወጣቶች) ከተገደሉ በኋላ ወላጆች ለሬሳ ገንዘብ ከፍለው እንዲወስዱ ሲገደዱ ገንዘብ ከፍለው ለመውሰድ ያልቻሉ ወላጆች ልጆች ሬሳ ግን የትም ተርቷል ።

ለምሳሌ ሄሮድስ በአረመኔነቱ ጭካኔ የተሞላበት ብዙ አስከፊና አስነዋሪ ድርጊቶችን ፈጽሟል ። ክርስቶስ መንግሥቱን ይነጥቀኛል በሚል ፍራቻ ተነሳስቶ ብዙ ህፃናትን አስባስቦ እሱን አገኘሁ መስሎት ህፃናቱን አስገድሏቸዋል አስከሬናቸውን ግን ለወላጆች እንዲሰጥ አድርጓል እንጂ ገንዘብ ክፈሉ አላለም ።

በቅዱስ ወንጌል እንደምናነበው ሄሮድስ ይህን ግፍ በሚፈጽምበት ጊዜ መልአኩ ዮሴፍን እናቱንና ሕፃኑን ይዘህ ወደ ግብፅ ሂድ ብሎታል እመቤታችንም ልጇን ከዚህ መከራ ለማዳን ስትል በየመንገዱ ብዙ መከራ እየደረሰባት ረኃቡንና ውሃ ጥሙን በመታገስ የሌሊቱን ቁርና ሐሩሩን በመቻል ወደ ግብፅ ተሰዳለች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም የሷንና የልጇን ስደት በየዓመቱ ጥቅምት ወር በጸሎትና በመዝሙር ታስባለች የሄሮድስን ጭካኔ በልጆቹ የተፈጸመውን ሞት እንዲሁም በወላጆቻቸው ላይ የደረሰውን ዋይታ ጭምር ከነታሪካቸው ታስታውሳለች ።

ወደ ሀገራችን ታሪክ መለስ ስንል በኢትዮጵያ ያሉ ወላጆችም ልባቸው ስለሻከረ ስለልጆቻቸው መሞትና መገደል አብዛኛዎቹ ልጆቻቸውን እየያዙ ትውልድ ሀገራቸውን ጥለው ቢሰደዱም ከፊሎቹ ግን የዚህ ዕድል ሊያጋጥማቸው አልቻለም ። ለነገሩማ ሄሮድስ እንኳን እንዳይለቀስላቸው አልከለከለም ይሄ ግን አስከሬን በእሳት እያቃጠለ የግፍ ዳንኪራ በመርገጡ የሕሊና እረፍት የሚጎናጸፍ ቢመስለውም ኢትዮጵያ ግን በልጆቿ ኀዘን በመጠበቧ ወደ ፈጣሪ እንባዋን ከማፍሰስ የዋይታ ድምጿን ከማቅረብ የተቆጠበችበት ጊዜ አልነበረም ።

ቢሆንም "ታላላቆችና ታናናሾች በዚህች ምድር ይሞታሉ ፣ አይቀበሩም ሰዎችም አያለቅሱላቸውም ያለው አምላካዊ ቃል ተፈጸመ ትን.ኤር ም. ፲፮ ቁ ፲፮ በቃሉ መሠረት አልተለቀሰላቸውም ፣ ድንኳን አልተተከለላቸውም ዳስም አልተጣለላቸውም እያለቀሰ ሙሾ ያደረገ እንዲቀጣ ታዞ ነበርና ። ሌላው ቀርቶ ምእመናን ወደቤተ እግዚአብሔር ሄደው በመጸለይ ይደርስባቸው ከነበረው ኀዘንና መከራ ለማድረግ ሲባል የአብያተ ክርስቲያናት ደጆች መዘጋት እንዲሁ ዋናቸው አንጀቷን ሲያቆስለው የኖረ አሳዛኝና አሳፋሪ ተግባር ነው ። ይህ ሁሉ ሲሆን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፣ በዓለም የሰዎች መብት ተከራካሪ ድርጅት ፣ በዓለም የቀይ መስቀል ማኅበር እንዲሁም በዓለም የታወቁ ድርጅቶች አቤቱታቸውን አልፎም ኀዘናቸውን ለነበረው አስተዳደር ቢያሰሙም ጆሮ ዳባ ልበስ ከማለት በቀር ሰሚ አላገኙም ። እንዲያውብቻ ለኢትዮጵያ ሕዝቦች እንጸልይ ሲሉ የጥሪ ደወላቸውን ለዓለም ሕዝብ ሲያስተጋቡ ልመናቸውንም ወደ እግዚአብሔር ሲያቀርቡ ቆይተዋል።

ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ዘርግታ ስትጸልይ ኖራ የሰላም ጭላንጭል ለማየት በቅታለች ። አሁንም የታየውን የሰላም ጭላንጭል ሙሉ በሙሉ ያስፍንላት ዘንድ ወደ እግዚአብሔር በጸሎት በምህላና በእንባ የዋይታ ድምጿን ከማቅረብና ከመለመን አታቋርጥም ያለሰላም መኖር አይቻልምና ።

## ፀዓተ ክረምት

(ከገጽ ፳፱ የዞረ)

ጥቂቶች አይደለንም ። ያለእርሱ ረዳትነትና ያለእርሱ ፈቃድ ሁሉን ማድረግ እንደማንችል በትክክል የተረዳን አይመስልም ። ሥራው ከተጣራ በኋላ እጥፍ ድርብ የሆነ ክብርን ይጐናጸፋል ። በዚያን ጊዜ ጻድቃን በአባታቸው መንግሥት እንደፀሐይ ያበራሉ ። ማቴ ፲፫ - ፵፫

ስለዚህ ገበሬው የክረምቱን ወራት ቁር የበጋውን ሐሩር ሳይፈራ ከዘር እስከመከር የደከመበትን የሥራ ፍሬ አግኝቶ እንደሚደሰት ሁሉ እኛም የዚህን ዓለም ውጣ ውረድ ታግሰን የሚደርስብንን ሥጋዊ ፈተና ሁሉ በመልካም ሥራ አሳልፈን ዘለዓለማዊ የሕይወት ፍሬን እንድናፈራ ይጠበቅብናል ።

መ መንክር ዋሲ.

# ጤናችን

## የወባ በሽታ

### የበሽታው ምንነት

ወባ እያጣደፈ አንዳንዴም እያለሰለሰ በመደጋገም ለብዙ ጊዜ የሚያሰቃይ ተላላፊ በሽታ ነው ። የበሽታው ምልክቶች ፣

፩/ ጠቅላላ የጤንነት ቀውስ
፪/ የሰውነት መቀረጣጠፍ
፫/ ብርድ ብርድ ማለት
፬/ ትኩሳት
፭/ ማንቀጥቀጥና በላብ መነከር
፮/ ማቅለሽለሽ ሃሞት ማስታወክ
፯/ የጣፊያ አንዳንዴ የጉበት ማበጥ (በተለይም በህፃናት ላይ)
፰/ የነዚህ ምልክቶች በየሁለት ቀን በየሶስት ቀን ወይም በየአራት ቀን መደጋገም ናቸው ።

የበሽታው ምክንያት ፕላስሞዲያ የተባሉ የደም ጥገኛ ረቂቅ ሕዋሳት ናቸው ።

የበሽታው ፅንስ እንደ ሕዋሳት ዓይነት ነው ቢሆንም ከ፲፪ እስከ ፴ ቀን ሊሆን ይችላል ። የበሽታው መኖሪያ ወይም ማኅደር የበሽታው ዋና ማኅደር ሰው ነው የበሽታው የቅርብ ምንጭ በበሽታው ሕዋሳት የተለከፈች ትንኝ ናት በሽታውን ለይቶ የማወቂያ ዘዴ ከበሽተኛው ጣት ላይ የደም ጠብታ ወስዶ ካዘጋጁ በኋላ በሚያጉላ መነፅር ሲመለከቱት ሕዋሳት ሊታዩ ይችላሉ ። የበሽታው መዛመቻ መንገድ እንስቲቱ የወባ ትንኝ በሌሊት የሠው ደም የመጠጣት ጠባይ አላት ትንኟ የወባ በሽታ የያዘውን ደም ስትጠጣ ከደሙ ጋር የበሽታውን ሕዋሳትም አብራ ትመጣለች እንደገና ደም ለመጠጣት ወደ ጤናማ ሰው ሄዳ በምትናከስበት ጊዜ ከበሽተኛው የወሰደቻቸውን ሕዋሳት በጤነኛው ሰው ሰውነቱ እንዲገቡ ታደርጋለች ሰውየው በዚህ ሁኔታ በበሽታው ይለከፋል ። የበሽታው የመተላለፊያ ወቅት የበሽታው ረቂቅ ሕዋሳት በሰው ደም እስካሉ ድረስ ነው ። ለበሽታው ተጋልጠው ሊያዙ የሚችሉት በሽታው ማንንም ሰው ሊይዝ ይችላል ሆኖም በይበልጥ ተጋልጦ ሊያዝ የሚችለው ቀደም ሲል ወባማ አካባቢ ያልኖረና በወባ በሽታ ተይዞ የማያውቀው ሰው ነው ።

በሽታው የሚገኝባቸው ቦታዎች በሽታው በዓለም ላይ ባንዳንድ ቦታዎች ከቁጥጥር ሥር ውሏል ቢባልም አሁንም በብዙ ቦታዎች ይገኛል ። በኢትዮጵያም እጅግ ለም በሆኑት ረባዳና ቆላማ ቦታዎች ይገኛል የበሽታው መከላከያ።

፩/ የታመሙትን ሰዎች ሁሉ እስኪድኑ ድረስ ማከም ፣
፪/ የሚቻል ከሆነ መስኮቶችን ትንኝ በማያስተላልፍ ጠቅጣቃ የሽቦ ወንፊቶች መጋረድ ፣
፫/ የትንኝ መራቢያ ሊሆኑ የሚችሉትን ኩሬዎች ሁሉ ቦይ በመክፈት እንዲደርቁ ማድረግ ፣
፬/ በመኖሪያ መንደሮች አካባቢ የሚገኙትን አረሞችና ቁጥቋጦዎችን መንጥሮ ማጥፋት ፣
፭/ ጠቃሚ ያልሆኑና ውሃ አቁረው ሊቆዩ የሚችሉትን አሮጌ ቁሳቁሶች ከመኖሪያ አካባቢ ማጥፋት ፣
፮/ ለረጅም ጊዜ ሊቆይ የሚችል ዲዲቲ ወይም ሌላ መድኃኒት በቤት ግድግዳዎች ላይ በመርጨት ትንኝን ማጥፋት ፣
፯/ የወባ በሽታ በወረርሽኝ መልክ ሲነሳ ለጤና ባለሙያዎች አስታውቆ በሽታውን በቁጥጥር ለማዋል ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ።
፰/ አጠር ላለ ጊዜ ወባማ ወደሆነ ሥፍራ ለሚሄዱ ሰዎች መከላከያ መድኃኒት በየተወሰነው ጊዜ ሳያቋርጡ እንዲወስዱ ማድረግ ፣

ማሳሰቢያ

ብሔራዊት ጥንታዊትና ፣ ታሪካዊት የሆነችው ቤተ ክርስቲያናችን አቅፈው ደግፈው ታሪኳን ለአዲሱ ትውልድ እንዲሁም ለመላው ዓለም አስደናቂ የሆነውን ቅርሳችንን ያቆዩት አባቶች ብዙውን ጊዜ የሚገኙት በቆላማ ቦታዎች ባሉ ገዳማትና አድባራት ነው ። እነዚህም ገዳማትና አድባራት የወባ ትንኝ (የወባ በሽታን የሚያመጡ ነፍሳት) በሚገኙበት ስለተመሠረቱ ብዙ አባቶች በወባ በሽታ ሲሰቃዩ መቆየታቸው ግልፅ ነው ።

ለምሳሌ ፣ በአበው አባባል አንዳንድ ጊዜ በዋልድባም ይዘፈናል መባሉ የሚያመለክተን በዚያ የሚኖሩ መነኩሳት በንዳድ መሰቃየታቸውን ነው ።

ስለዚህ ሃይማኖት እንዳባቶቻችን ሥልጣኔ እንደዘመናችን ነውና በየወረዳውና በየአውራጃው ያሉ የሰበካ ጉባኤ አባላትና የኀብረ ማኅበራት በየአካባቢያቸው ከሚገኙ የጤና ጥበቃ ሠራተኞች ጋር በመተባበር በሽታውን አስተላላፊ የሆኑ ትንኞች ያሉበትን ቦታ ለማፅዳት ለኅብረተሰቡ ትምህርት መሥጠት አለባቸው ።

መላከ ሕይወት ይትባረክ ዓለሙ



www.ethiopianorthodox.org

# ጻአተ ክረምት

የዘመናት አቆጣጠር በተለያዩ ዓለማት ልዩነት ቢኖራቸውም ይቂቃ በሰዓት ፡ ሰዓት በዕለት ፡ ዕለት በሳምንት ፡ ሳምንት በወራት ፡ ወራት በወቅት ፡ ወቅትም በዓመታት መጠቃለላቸው በሁሉም ዘንድ የተረጋገጠ ነው ። ይኸውም በአንድ ዓመት ውስጥ አራት ወቅቶች ፲፪ ወራትና ፫፻፷፭ ¼ ቀኖች አሉ ማለት ነው ።

የወቅቶች አከፋፈል ደግሞ ከመስከረም ፳፮ ቀን እስከ ታኅሣሥ ፳፭ ድረስ ዘመነ መፀው ፡ ከታኅሣሥ ፳፮ እስከ መጋቢት ፳፭ ቀን ዘመነ ሐጋይ ፡ ከመጋቢት ፳፮ እስከ ሰኔ ፳፭ ቀን ዘመነ ፀደይ ከሰኔ ፳፮ እስከ መስከረም ፳፭ ዘመነ ክረምት በመባል በ፺ (ዘጠና) ቀን ተከፋፍለዋል ።

ወደ አለንበት ወቅት (ዘመነ መፀው) መለስ ስንል ቀደም ብሎ ከሰኔ ፳፮ ቀን ጀምሮ በአተ ክረምት (የክረምት መግቢያ) እንደተባለ ከመስከረም ፳፮ ጀምሮ ያለው ጻአተ ክረምት (የክረምት መውጫ) ተብሎ ይጠራል ። ይህንንም የሚመስል ቃል ጻአተ ግብፅ" የሚል አነጋገር አለ ይህም የእሥራኤልን ከግብፅ ግዛት አርነት መውጣት የሚገልጽ እንደመሆኑ ጻአተ ክረምት የሚለውም ቃል ከክረምቱ ዶፍና ትዝታዜ ፡ ድጥና ማጥ ወጥቶ ሞቃትና ምቹ ወደሆነው ዘመን መጸው መሸጋገርን ያበሥራል ።

አራቱም ወቅቶች የተለያዩ የአየር ጠባይዎች ስለአሉዋቸው የተለያዩ ተግባራት ይከናወኑባቸዋል። ጠል ለምድር ዘር ለመከር "እንደሚባለው የክረምት ወራት የደመናና የዝናም ጊዜያት እንደመሆናቸው የዘር የጉልጓሎና የአረም ሥራ ይካሄዱባቸዋል ። የመፀው ወራት ደግሞ ነፋሻና ፀሐያማ ስለሆኑ የመከር ወራት በመባል የማጨድ ፡ የመከመርና የመውቃት ሥራዎች በነዚህ ጊዜያት አመቺ ናቸው ። ገበሬው ዝናቡንና ብርዱን ታግሦ ዘሩን ከጐተራ እያወጣ በሚዘራበት ጊዜ ብዙ ድካምና ኀዘን ቢሰማውም በመከር ወራት ግማሹ አሽቶ ግማሹ ጐምርቶ ሌላውም ታጭዶና ተከምሮ እያየው ውድማ የገባውንም እየወቃ ሲያስገባ ለደስታው ወሰን የለውም" በኀዘን የሚዘሩ በደስታ ይለቅማሉ ፡ በሄዱ ጊዜ ዘራቸውን ተሸክመው እያዘኑ ተሰማሩ በተመለሱ ጊዜ ግን ነዶአቸውን ተሸክመው ደስ እያላቸው ይመለሳሉ፡ መዝ ፡ ፻፵፯፡፰—፱

ክፉን ከልተወጡት ደግ አይገኝምና በዚህ ዓይነት ሦስት ወር ሙሉ ሌት ከቀን ደክሞ ባስገኘው ምርት ከራሱ አልፎ ለወገን ተርፎ ለተራበ አብልቶ ለተጠማ አጠጥቶ በመኖሩ ደስታው በዚህ ዓለም ብቻ ሳይሆን በወዲያኛውም ዓለም ዘለዓለማዊ ይሆንለታል ። የመፀው ወራት ለሰው ልጆች ብቻ ሳይሆን ለእንስሳት ለአራዊትና ለአዕዋፋትም ምቹና የደስታ ወቅቶች ናቸው በክረምት ወራት የለመለመው ሣር ጠፋፍ ሲልላቸው እየጋጡ የጠራውን ውሃ እየጠጡ በሮች ሲያገሱ ላሞች ወተታቸውን እንደልብ ሲለግሱ ጥጆች ሲፈነጥዙ ማየቱ የሁሉም ተሐድሶ ነው አዕዋፍም ከየዋሻቸው በመውጣት የዕፀዋትን ፍሬ እየለቀሙ በአማረ ጣዕመ ዜማቸው ፈጣሪያቸውን ያመሰግናሉ ንቦችም በተፈጥሮ በተሰጣቸው ልዩ ዕውቀት የተለያዩ አበቦችን በመቅሰም እጅግ ጣፋጭ የሆነ ማርን ሠርተው ለሰው ልጆች የሚያበረክቱት በዚሁ ጊዜ ነው ።

ምድር በተለያዩ አበባዎች አሸብርቃ ከአረንጓዴነት ወደቢጫነትና ሐምራዊነት በመለወጥ ተመልካቾችን ትማርካለች የአበቦች ኅብረ ቀለም በጥራቱና በአይነቱ ጥበበኞች ከቀመሙት የቀለም ዓይነት ይልቅ በውበታቸው ዓይንን ይስባሉ መድኃኒታችን ክርስቶስ ወንጌልን ሲያስተምር አበቦችን ምሳሌ በማድረግ "ሰሎሞን እንኳ በክብሩ ብዛት ከእነዚህ አበቦች እንደ አንዱ አልለበሰም" ሲል የአበቦችን አስደናቂ ውበት ገልጿል ማቴ. ፮—፳፱ ።

ይህ ወቅት ገበሬዎች የድካማቸውን ፍሬ የሚያገኙበት ፡ ርኁባን የሚጠግቡበት የተጠሙ የሚረኩበት ፡ በጠቅላላው የሰው ልጆች ሁሉ የምድርን በረከት አግኝተው የሚደሰቱበት ወቅት በመሆኑ ሁላችንም ከሌሎቹ ወቅቶች አብልጠን በተስፋ የምንጠብቀው ጊዜ ነው ታዲያ ምድር ያበረከተችልንን ፍሬ እየተመገብን መኖር ብቻ በቂ አለመሆኑን መረዳት አለብን "ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው ቃል ሁሉ በሕይወት እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም" (ዘዳ. ፰—፫) በሚለው መሠረት በምግባር አብበን በሃይማኖት ጸንተን የሕይወት ፍሬን እንድናፈራ ያዝዘናል ።

እግዚአብሔር አምላክ ቃል ኪዳኑን ሳይረሳ ወቅቶችን ክረምትና በጋን እያፈራረቀ በዝናም አብቅሎ በፀሐይ አብስሎ ይመግበናል ። ነገር ግን በራሳችን ጥረትና ድካም ብቻ ሠርተን በማግኘት መኖር የምንችል የሚመስለን

(ወደ ገጽ ፳፪ ይዞራል)



# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የሰብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፡

ማኅሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፡

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፡ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፡ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ ላላቀረቡ ግን ስምንት ብር በማስከፈል ይሰጣል ። ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የሰብከተ ወንጌልና ሐዋሪያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፡

የስልክ ቍ.
የመልእክት ሣ.ቍ. 3137
አዲስ አበባ ፡

www.ethiopianorthodox.org